መልካም·አዲስ·ዓመት




ሕገ ወጡ ሕግ
ገጽ 11

ባልደራስና የዐቢይ መንግሥት ገጽ 5

# ባልደራስ

1ኛ ዓመት ቁጥር 01 መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም.









## የእነ እስክንድር መልዕክት ከእስር ቤት

አርሶ አደሮች ግብር ላለመክፈል ወሰኑ ገጽ 4

ከታሪክ ሽሚያ እስከ ወረራ ገጽ 7

የአዲስ አበባ ት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን መንግሥት ሊከሱ ነው

# የአዲስ አበባ ራስ ገዝ አስተዳድር ይመስረት

አዲስ አበባ ወደ ራስ ገዝነት እንድታድግ የሁላችንንም ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል!

ህብረ ብሄራዊትና የኢትዮጵያችንን መልክ የያዘችው ከተማችን አዲስ አበባ በአንድ  ጽንፈኛ የዘውጌ ብሔርተኛ የምትገዛበት ሕገ ወጥ አካሄድ በፍጥነት ሊቆም ይገባል፡፡ አዲስ አበባ ካላት ግዝፈትና ከዋና ከተማነቷ አንጻር የራስ ገዝነት ደረጃ እጅግ የሚመጥናት ከተማ ናት።

የብሄር ፌዴራል ስርአቱ ሲዘረጋና ቅርጻ መንግስቱ ሲዋቀር በብሄሮችና በብሄራዊ ማንነት መካከል የፈጠረው የትስስር መርሆ የሚያናቁር ከመሆኑም በላይ ቅርጻ መንግስቱ በተለይ አዲስ አበባን ለከፍተኛ መዋቅራዊ ችግሮች ዳርጎብናል።  የክልል ሥርዓቱ አማራን ከትግራይ፣ ሶማሌን ከኦሮሞ፣  ወዘተ ሲከልል በዜጎች መካከል አጥር አበጅቶ የዜግነትን ለዛውን ከማጥፋቱም በላይ የኢትዮጵያውያን የጋራ ከተማ የሆነችውን አዲስ አበባን ወደ ልማትና እኩልነት እንዳትዘረጋ አሜኬላ ሆኖባት እስካሁን ይኖራል።

ከፍተኛው የኢትዮጵያችን የገበያ ድርሻ የሚንቀሳቀስባት እና ከሰባት ሚሊዮን ባላይ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩባት ከተማችን አዲስ አበባ በጥላቻ በሰከሩ ጥቂት ቡድኖች ቁጥጥር ስር ወድቃብናለች፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግሮቿ ማስታመም አልበቃ ብሏት በጽንፈኞች መሪዎች የገመድ ጉትቻ መከራዋን ታያለች።

ሕገ መንግሥቱ ራሱ  በአንቀፅ 69 ላይ ‹‹የፌዴራሉ መንግሥት ርዕሰ ከተማ አዲስ አበባ ነው፡፡ የከተማው አስተዳድር ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡›› ይላል፡፡ ታዲያ ከተማዋ ራሷን በራሷ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን እንዳላት ቢታወቅም ‹‹በአዲስ አበባ ከተማ የኦሮሚያ ክልል ልዩ ጥቅም ይኖረዋል፡፡›› የሚል የእኩልነት ተጻራሪ አንቀጽ ሰንቅረው ከተማችንን ደረጃዋን የጠበቀች ዓለም አቀፍ ከተማ ከማድረግ ይልቅ  ስንናቆር እንድንኖር አድርጓል፡፡ ዛሬ ከሁሉም የከፋው ደግሞ ከባለፈው ጊዜ ስህተት ሳይማሩ ቀርተው የተረኝነት አባዜ የተጠናወታቸው መሪዎች ከተማይቱን ወደ እኩልነት ጎዳና ሳይሆን ወደ ልዩ ጥቅም ፍለጋ ጎዳና እየወሰዱ መሆናቸው እጅግ አሳሳቢ ነገር ሆኗል።

ዛሬ አዲስ አበባ ከመቼውም ጊዜ በላይ በከፋ ደረጃ ስጋት ውስጥ ትገኛለች። የሕልውና ስጋት ላይ ነች፡ ፡ ስለዚህ የራስ ገዝ አስተዳድርነቷ እንዲከበርና ወደ እኩልነት ጎዳና መሪዋን እንድታዞር ሁላችንም ለትግል ቆርጠን መነሳት ይኖርብናል፡፡ ይህንን ትግል መላው የኢትዮጵያ ህዝብም ሊደግፈው ይገባል። የአዲስ አበባ የመዋቅር ጥያቄ በሃገራችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣውን የዘውግ ፖለቲካ ለመለወጥ እርሾ ነው። አዲስ አበባ በተለያዩ መዋቅራዊ ችግሮች ተተብትባ ብትቆይ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ለውጥ ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ ጉልህ ሲሆን በአንጻሩ አዲስ አበባ የምታሳያቸው በጎ ለውጦች በኢትዮጵያ በጎ ለውጥ ላይ ሚናው ጉልህ ነው።

ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ በአዲስ አመት ዋዜማ ላይ አዲስ አበባ ወደራስ ገዝ አስተዳደርነት ታድግ ዘንድ ትግሉን ከፍ ወደ አለ ምዕራፍ አሳድጎ እንቅስቃሴውን ጀምሯል። በመሆኑም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪክ ድርጅቶችና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ትግል በመደገፍ አዲስ አበባን ማዳን ይጠበቃል።

መልካም አዲስ ዓመት!

**ባልደራስ ጋዜጣ**
መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም.
ተመሰረተ

በየ15 ቀኑ የሚታተም

**አሳታሚ**
የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ
ፓርቲ (ባልደራስ)

**ዋና አዘጋጅ**
ጌጥዬ ያለው
ክፍለ ከተማ፡- ቂርቆስ
ወረዳ፡- 02 የቤት ቁጥር፡- አዲስ
ስልክ፡- +2519 24 51 70 77
ኢ-ሜይል፡- newsgett@gmail.com

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ወግደረስ ጤናው

**አምደኞች**
ገለታው ዘለቀ
ኢንጂነር ጌታነህ ባልቻ

**አርታዒ**
መሰበወርቅ ቅጣው
ነብዩ ውብሸት

**ፀሐፊ፡-** ሕይወት ዳዊት


**የገፆች ቅንብር** ሐብ-ዲዛይን

**ገፀ ድር አስተዳደር** ኢስያስ ፅጉ









# እስክንድር ነጋና የትግል አጋሮቻቸው ከእስር ቤት ያስተላለፉት መልዕክት

ፕሬዚደንቱ አቶ እስክንድር ነጋን ጨምሮ በግፍ እስር ቤት ውስጥ የሚገኙ የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) አመራሮችና አባላት ተከታዩን የአዲስ አመት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡-

*. . . እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፡፡ ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል፡፡*

*፩ኛ ቆሮንጦስ*

*ምዕራፍ ፲ ቁጥር ፲፪ እና ፲፫*

**ውድ ኢትዮጵያውያን እንኳን አደረሳችሁ! መልካም አዲስ ዓመት!**

# የአዲስ አበባ ት/ቤቶች ርዕሳነ መምህራን መንግሥት ሊከሱ ነው

በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን በገፍ ከደረጃቸው ዝቅ መደረጋቸውን ተከትሎ መንግሥትን ለመክሰስ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን አስታውቀዋል። ርዕሳነ መምህራኑ ከደረጃ ርከናቸው ዝቅ በማለት መምህራን ወይም ደግሞ አስተባባሪዎች እንዲሆኑ የከተማዋ ትምህርት ቢሮ ትዕዛዝ አስተላልፏል። ቢሮው ከወራት በኋላ ግን ነባሮቹ ከአዳዲስ ርዕሳነ መምህራን ጋር ተወዳድረው ብቃታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ለነበሩበት የሓላፊነት መደብ የሚመጥኑ ከሆነ ብቻ ባሉበት እንደሚቀጥሉ ነግሯቸዋል። ይሁን እንጂ ጉዳዩ ከኦሮሞ ተወላጆች ውጭ በሆኑት ላይ ያነጣጠረ ማንነት ተኮር ጥቃት እንደሆነ ርዕሳነ መምህራኑ ገልፀዋል። «ድርጊቱ ኦሮምኛ ተናጋሪ አዳዲስ ርዕሳነ መምህራንን በቦታው ለማስቀመጥ ያለመ ነው። መንግሥት ደሞዛችንን ከመቀነሱም በላይ ሞራላችንን ነክቶታል። ሥራውን ጥለን እንድንወጣም ጫና እየተደረገብን ነው።» ብለዋል። በአሁኑ ጊዜ ከፊሎች በጫናው ተሳቀው ትምህርት ቤቶችን ለቀው የወጡ ሲሆን ከፊሎች ደግሞ ከደረጃቸው ዝቅ ብለው በመምህርነት እያገለገሉ ይገኛሉ። ሌሎች ቀሪዎችም በአስተባባሪነት እንዲሠሩ ተገደዋል።

ይህንን ተከትሎ ርዕሳነ መምህራኑ መንግሥትን ለመክሰስ እየተንቀሳቀሱ ነው። የአዲስ አበባ ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ በቀጥታ የሚከሰሰው የመንግሥት ተቋም መሆኑንም ከሳሾች ገልፀዋል። ከዚህ በፊት ክሱን ለመመስረት ወደ ፍርድ ቤት ያመሩ ቢሆንም «በትስማሙ ይሻላል። እንደገና አስቡበት» ተብለው ክሱን ሳይመሰርቱ መመለሳቸውን ጠቁመዋል።

በከተማዋ 188 የመንግሥት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ያሉ ሲሆን 160ዎቹ ሴቶች ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ የኦሮምኛ ትምህርት በቅንጅት በሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች የሚሰሩ ርዕሳነ መምህራንም ኦሮምኛ ተናጋሪዎች እንዲሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስገዳጅ መመሪያ አውጥቷል። በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ርዕሰ መምህሩ ወይም ምክትል ርዕሰ መምህሩ ኦሮምኛ በአግባቡ መናገር፣ መስማት መፃፍና ማንበብ የሚችል እንዲሆን መመሪያው ያስገድዳል። በተመሳሳይ የኦሮምኛ ትምህርት በሚሰጥባቸው የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የገዳ ድርጅታዊ ትምህርት እንደሚሰጥም የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አስታውቋል። ሆኖም ገዳ ወረራ፣ ግድያና ዘውጌ ብሔርተኝነትን መለያው ያደረገ እንደሆነ በዘርፉ የተመራመሩ ምሁራን ይገልፃሉ።

ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማህበር መንግሥት የሕግ የበላይነትን ባለማክበሩ መንግሥትን ለመክሰስ ሲንቀሳቀስ መቆየቱ አይዘነጋም። በአዲስ አበባ ፖሊስ ጣልቃ ገብነት የክስ እንቅስቃሴው መቋረጡም አይዘነጋም። በተመሳሳይ ከደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ወደ ትውልድ ቀያቸው ሲጓዙ በሸብር ቡድን የታገቱ የአማራ ተማሪዎችን ጉዳይ በተመለከተ ሴት ኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማህበር የአብይ አሕመድን መንግሥት ለመክሰስ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወሳል።

# የአዲስ አበባ የነዋሪነት መታወቂያ

## ቦረና ለሚኖሩ እየተሰጠ ነው



የአዲስ አበባ ከተማ የነዋሪነት መታወቂያ በሕገ_ወጥ ሂደት ቦረና ዞን ሞያሌ ከተማ ለሚኖሩ የኦሮሞ ተወላጅ የመንግሥት ሠራተኞች እየተሠጠ መሆኑን የአካባቢው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ጠቁመዋል። በአካባቢው ማለትም ያቤሎ ቅርንጫፍ ስቱዲዮ ለሚሠሩ የኦሮሞ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ (ኦ ቢ ኤን) ሰራተኞችም ሕገ ወጥ መታወቂያው ባሉበት ተሰጥቷቸዋል። ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከ30 በላይ ለሚሆኑ የቦረና ነዋሪወች ወደ አዲስ አበባ ሳይመጡ ባሉበት እንደተሰጣቸውም ከውስጥ ምንጮች የደረሱን መረጃዎች ያመላክታሉ።

እንደ አካባቢው የመረጃ ምንጮች ገለፃ ለኦ.ቢ.ኤን. ሠራተኞች የተሰጠው መታወቂያ አላማው ሠራተኞችን በአዲስ አበባ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማደል ነው። ለሌሎች እየታደለ ያለው ደግሞ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ኦሮሞዎች በመጭው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ለማሳተፍ ያለመ እንደሆነም ተናግረዋል። ቦረና ከአዲስ አበባ በ575 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል።

# ግብር ባለመክፈል መንግሥትን እንደሚቃወሙ የአዲስ አበባ አርሶ አደሮች ተናገሩ

ለኦሮሞ ተወላጅ አርሶ አደሮች ብቻ ተለይቶ የጋራ መኖሪያ ቤት መሰጠቱትን የገለፁት አርሶ አደሮቹ «በከተማችን እኩል ተጠቃሚ የማንሆን ከሆነ የመሬትም ሆነ የሥራ ግብር አንከፍልም።» ብለዋል። አርሶ አደሮቹ ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ ድረስ እንደነገረቤቶቻቸው ሁሉ ለእነርሱም የጋራ መኖሪያ ቤት እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም ኦሮሞ ባለመሆናቸው ብቻ እንደከለከሏቸው ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል። ‹እንዳውም የያዛችሁት የእርሻ መሬት የአያቶቻችን ነው። ትመልሳላችሁ› መባላቸውንም ተናግረዋል። «ቤቱ እንዲሰጠኝ መጀመሪያ ስጠይቃቸው መታወቂያዬ ላይ ብሔሬን አይተው ሰድበው ሰደዱኝ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ብሔር የሌለውን አዲሱን መታወቂያ አውጥቼ ስሄድ አሁንም ስሜን አይተው ከለከሉኝ።» ብለዋል ዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው አርሶ አደር።

የቀድሞው ምክትል ከንቲባ አቶ ታከለ ኡማ ለኦሮሞ ተወላጅ አርሶ አደሮች ትራክተር በነፍስ ወከፍ ሲያድሉ ለእነርሱ እንዳልተሰጣቸውም ቅሬታ አቅራቢዎቹ ገልፀዋል። ከግብርና ሥራቸው በተጨማሪ አነስተኛና መካከለኛ የንግድ ሥራዎችንም እንደሚሠሩ የገለፁት ነዋሪዎቹ



አንዳች ግብር ለመንግሥት እንደማይከፍሉም ተናግረዋል። ከዘንድሮው የግብር ዘመን ጀምሮ ላለመክፈል ለራሳቸው ቃል መግባታቸውን ገልፀዋል። አርሶ አደሮቹ ከከተማ ግብርና ፕሮጀክትም ተገልለዋል።

# ባልደራስና የዐቢይ መንግሥት

ሕወሓት ማዕከላዊ መንግሥቱን ለ27 ዓመታት ተቆጣጥሮ ከነበረበት የሥልጣን መደላድል ተንሸራቶ ሊወጣ ተቃርቦ የነበረበት ጊዜ ነው። ደህንነቱን ጨምሮ የተለያዩ የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ሚስጥሮች እንደማያውቁ የተናገሩት የደኢሕዴኑ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የጠቅላይ ሚንስተርነት ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው መልቀቃቸውን ይፋ አደረጉ። ከዚህ ቀን አንድ ወር፤ ምናልባትም ሳምንታትን ቀደም ብሎ ያደረጓቸውን ንግግሮች ለመረመረ ሰው ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንደሚለቁ ርግጠኛ መሆን ባይቻልም በሕወሓት አለቆቻቸው ልባቸው እንዳበጠ አመላካች ነበር። በወቅቱ ጋዜጠኛ እና የሰብአዊ መብት ተሟጋች እስክንድር ነጋን ጨምሮ የፖለቲካና የሕሊና እስረኞች እየተፈቱ ነበር። ይህንን አስመልክቶ አቶ ኃይለማርያም ባደረጓቸው ንግግሮች ሁሉ ‹‹የፖለቲካና የህሊና እስረኞች›› እያሉ ነበር የሚገልፁት። መንግሥታቸው ለዘመናት ሁሉም እስረኞች በወንጀል የተጠረጠሩ እንጂ በፖለቲካ አመለካከቱ የታሰረ አንድም የህሊናም ሆነ የፖለቲካ እስረኛ እንደሌለው ሲያውጅ መቆየቱ አይዘነጋም። በአሻንጉሊትነት የሚታወቁት ጠቅላይ ሚንስትር ይህንን ሲንዱት ድብብቆሹ መጠንከሩን ለመረዳት አያዳግትም። የወቅቱ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና የዛሬው የአብይ አሕመድ የሕግ ጉዳዮች አማካሪ አቶ ጌታቸው አምባዬ የህሊናና የፖለቲካ እስረኞችን መፈታት አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጡ። አንድም የፖለቲካና የህሊና እስረኛ እንደሌላቸው በመግለፅ የመንግሥታቸውን አቋም አስረገጡ። የጠቅላይ ሚንስትሩን ስህተት ለማረም በሚመስል መልኩ ደጋግመው ተናገሩት። ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ስማቸው እምብዛም በአደባባይ የማይታወቀው አብይ አሕመድ ጠቅላይ ሚንስትር ሆነው መጡ። ‹‹አሸባሪዎች እኛ ነን›› በማለት ወንጀሎቻቸውን በፓርላማው ፊት ተናዘው ፓርላማው ውስጥ ደብዝዞ የነበረውን የኢትዮጵያዊነት ስሜት በመቀስቀሳቸው አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ሕዝባዊ ቅቡልነትን አገኙ። እስረኞች በብዛት ተፈቱ። በኤርትራ መሽገው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስማቸው ከሽብር መዝገብ ተፍቆ ወደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተላለፈ። ሞቅ ባለ አቀባበል ከእነ ጦር ሰራዊታቸው ሀገር ውስጥ ገቡ። አብይ አሕመድ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ የፖለቲከኞችን መሪዎች በቀይ ምንጣፍ ሲቀበሉ አቦይ ስብሃት ነጋ ደግሞ የኤርትራ አዋሳኝ ድረስ ዘልቀው የኦነግ ጦር ሰራዊትን አርማውን እያውለበለቡ ተቀብለውታል። እነኝህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከጦር ሰራዊታቸው በተጨማሪ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂንም ይዘው ነው የመጡት።

## የአዲስ አበባ ባለአደራ ምክር ቤት

ከዚህ በኋላ የአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ፖለቲካ ውጥንቅጡ ወጣ። ሕዝብ በተሰበሰበበት የግጥም ምሽት ሁሉ ድንገት ይገኙ የነበሩት፣ መኪና እያሽከረከሩ በከተማዋ ይንቀሳቀሱ የነበሩት ጠቅላይ ሚንስትር ‹‹አምቦ ከሄድኩ እገደላለሁ›› ‹አጥሬን አጥብቁ› ማለት ጀመሩ። እንደ ሩሲያው ቭላድሚር ፑቲን ካልሆንኩ ያሉት አብይ በወራት ልዩነት እንደ ቀድሞ አለቃቸው መለስ ዜናዊ አጥር አጥባቂ ሆነው አረፉት። የራሳቸውን ጠባቂ ሠራዊት ‹ሪፐብሊካን ጋርድ› በሚል አደራጁ። ማንነቱ ካልተገለፀ ሀገር በቅርቡ ሰልጥነው የመጡ አዳዲስ አባላትም እንደተጨመሩለት ይፋ ተደርጓል። ከዚህ ዜና አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ጠቅላይ ሚንስትሩ ሳዋ የተባለውን የኤርትራ ወታደሮች ማሰልጠኛ መጎብኘታቸው ይታወሳል። ስለዚህ የሪፐብሊካን ጋርድ አባላቱም በኤርትራ እንደሰለጠኑ መገመት ይቻላል። ጠቅላይ ሚንስትሩ እንዲህ የራሳቸውን አጥር ሲያጠብቁ ኢትዮጵያን ግን ከጥቃት መከላከል አልቻሉም። የዘወትር ሥራቸው አስከሬን ቆጠራ ሆኗል። ታዲያ የወቅቱ የፖለቲካ ውጥንቅጥ ቀዳሚ ዱላውን ያሳረፈው አዲስ አበባ ላይ ነው። ከተማዋን ወደ ኦሮሚያ ለመጠቅለል እንቅስቃሴዎች ተፋፍመው ቀጠሉ። ጠቅላይ ሚንስትሩ ግን ያን ጊዜም ሆነ ዛሬ ስለ አዲስ አበባ በአማርኛ ያሉት ነገር የለም። በእርግጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለ ከተማዋ ፍርሰት ብዙ እንደዶለቱ ይነገራል።

የከተማው ሕዝብ ስለሚኖርባት አዲስ አበባ እንዲነጋገር አቶ እስክንደር ነጋ ስብሰባ ጠሩ። አዲስ አበባ፤ ባልደራስ አዳራሽ በሕዝብ ሞልቶ ተጥለቀለቀ። አዳራሹ አልበቃ ብሎ ብዙ ጊዜ ለሰርግ እና መሰል ዝግጅቶች የሚያገለግለው ግቢ በቆሙ ሰዎች ሞልቶ ነበር። ከግቢ ውጭም ወደ ውስጥ ለመግባት ወረፋ የሚጠብቁ ሰዎች ተሰልፈዋል። ይህ ሕዝብ የአዲስ አበባ ባለ አደራ ምክር ቤት እንዲቋቋምና በሚኖርባት ከተማ እኩል ተጠቃሚ እንዲያደርገው በፊርማው አደራ ሰጠ። ሆኖም የአዲስ አበባ ባለአደራ ምክር ቤት ሕዝብ የሰጠውን የከተማዋን መብት የማስጠበቅ ሥራ በነፃነት መወጣት አልቻለም። አንድ የሲቪክ ተቋም ታላላቅ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን አንግቦ በዚህ ደረጃ መንግሥትን እና ገዥውን ፓርቲ ሲሞግት ማየት ለኢትዮጵያ ፖለቲካ በተለይም ለኢሕአዴግ እንግዳ ነበር። በውጭ ሀገራት የሚኖሩ መሰል ተቋማት ይኖሩ ይሆናል። ከተማ ሙሉ ሕዝብ ሰብስቦ በአገር ቤት ሲደረግ ግን የባልደራስ እንቅስቃሴ የመጀመሪያው ነበር ማለት ይቻላል። ይህ ዕለት የአዲስ አበባ ወጣቶች መድረኩን ከማስተናበር በተጨማሪ ሰላም የማሥከበር ሥራውንም በብቃት የተወጡበት ነበር። አቶ እስክንድር ወደ አዳራሹ ሲመጡ ታዳሚያን በደስታ ከማቀፍና ከመደገፍ በተጨማሪ በትከሻቸው እየተሸከሚቸውም ጭምር ነበር ድጋፋቸውን የገለፁት።

የጠቅላይ ሚንስትር አብይ አሕመድ መንግሥት አምባገነናዊነት ከዚህ ጀምሮ ነው እየታወቀ የመጣው። ጠቅላይ ሚንስትሩ የባለአደራ ምክር ቤቱን ስብሰባዎችና ጋዜጣዊ መግለጫዎች በተደጋጋሚ በፖሊሶቻቸው አስከልክለዋል። በራስ ሆቴል፣ በኢትዮጵያ ሆቴል፣ በሒልተን ሆቴል እና በተቋሙ ፅህፈት ቤትም ጭምር መግለጫዎች ተከልክለዋል። ይህም ሆኖ ተቋሙ መንገድ ላይ ቆሞ መግለጫዎችን በመሥጠት ዛሬ የተንሰራፋው መንግሥታዊ የመሬት ወረራ እየተጀመረ መሆኑን ለሕዝብ አሳውቋል። የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ዝርፊያ እና የአዲስ አበባን የሕዝብ ስብጥር ቅየራ አጋልጧል። ዛሬ የተከሰተው ብሔርን እና ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ ጅምላ ጭፍጨፋ ሊከሰት እንደሆነ አስቀድሞ ተናግሯል። ‹ቄሮ› የተባለው የኦሮሚያ ወጣቶች አደረጃጀት ሁለት መልክ እንዳለውም አብራርቷል። አንደኛው ሰላማዊ ሲሆን ሁለተኛው

ደግሞ በአቶ ጃዋር መሐመድ የሚመራና አጥፊ ቡድን መሆኑን ለያይቶ አስረድቷል:: ይህ ፅንፈኛ ቡድን ጅምላ ጭፍጨፋ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆኑንን እና የጅምላ ጨፍጫፊነት ምልክቶችን ማየቱንም ባልደራስ በወቅቱ ለሕዝብ፣ ለመንግሥት፣ ለአለማቀፉ ማሕበረሰብ እና ለሌሎችም አሳውቋል:: ይህ ቡድን በሽብርተኝነት እንዲፈረጅና መንግሥት አስቀድሞ ጥቃቱን እንዲከላከልም ጠይቋል:: ሆኖም የጠቅላይ ሚንስትር አብይ ምላሽ በባልደራስ ላይ ጦርነት ማወጅ ሆነ::

## ጉዞ ወደ ፖለቲካ ፓርቲነት

የአዲስ አበባ ባለአደራ ምክር ቤት የሲቪክ ተቋም ሆኖ ለመቀጠል ከመንግሥታዊው የበጎ አድራጎትና ማሕበራት ኤጀንሲ ፈቃድ ቢጠይቅም አልተሰጠውም:: ይልቁንም እንቅስቃሴዎቹ ሁሉ በየጊዜው ይታገዱበት ነበር:: ሆቴል የተከለከለውን መግለጫ ቤተመንግሥት ውስጥ እንዲሠጥም መንግሥት ጠይቆት ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ አደረጃጀቱን ወደ ገዥው ፓርቲ አስተሳሰብ ለመውሰድ የሚደረግ ጥረት በመሆኑ ሳይቀበለው ቀርቷል::

ከአንድ አመት በፊት አዲስ ወግ በተሰኘው እና በጠቅላይ ሚንስትር ፅህፈት ቤት በተካሄደ የቤተ መንግሥቱ ቤተኞች (ሎሌዎች ላለማለት ነው) ስብሰባ ላይ ጠቅላይ ሚንስትሩ እንዲህ አሉ፡ - ‹‹የሚቀጥለው ምርጫ ፍፁም ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን እፈልጋለሁ:: አብርሃ ደስታ ካሸነፍክ በ24 ሰዓታት ውስጥ አቅፌ አስረክብሃለሁ:: ሳታሸንፍ አሁን ባለአደራ፤ አደራ እንደሚባለው አይነት ጨዋታ የምትጫወት ከሆነ ግን ግልፅ የሆነ ጦርነት ውስጥ እንገባለን ማለት ነው:: ይሄ መታወቅ አለበት:: የፖለቲካ አቋም ያለው ሰው ቢፈልግ በግሉ፤ ቢፈልግ በፓርቲ መወዳደር ይችላል::›› ኮሎኔል አብይ አሕመድ በዚህ ንግግራቸው ባልደራስ ላይ ጦርነት አወጁ:: ምርጫውም ተራዘመ:: መቼ እንደሚደረግ አይታወቅም:: የጓደኛቸው ኢሳያስ አፈወርቂን ልምድ በመጋራት ፈፅሞ ለመተውም ሳይዳዳቸው አልቀረም:: ጥርጣሬ አለ::

በዚህ ንግግራቸው ባልደራስ በሲቪክ ተቋምነት መቀጠል አይችልም:: ክልከላቸውን ተከትሎ የተገኘውን ዕድል ሁሉ አሟጦ ለመጠቀም በአዲስ አበባ ‹ክልል› ውስጥ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኗል:: ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) ተመሰረተ:: ነገር ግን ይህም እንደ ሌሎቹ ፓርቲዎች በሰፊ አዳራሽ ውስጥ በተረጋጋ ሁኔታ የተመሰረተ አይደለም:: መስራች ጉባኤውን ለማካሄድ ለኢንተርኮንቲነታል ሆቴል የአዳራሽ ኪራዩን ከፍሎ ዝግጅቱ ካለቀ በኋላ በጧት ተሰብሳቢዎችም ሆኑ አስተባባሪዎች ወደ ሆቴሉ እንዳይገቡ ፖሊስ ከለከለ:: የፖሊስ አዛዡም ጉዳዩ የበላይ ትዕዛዝ መሆኑን ከመግለፅ ውጭ ሌላ ማብራሪያ አልሰጡም:: ወደ ሆቴሉ የመጣው ጉባዔተኛ የሆቴሉ በር ላይ እስከ አስፋልት መንገዱ ማዶ ድረስ በመሰብሰብ በጉባዔ ፓርቲውን መሰረተ:: መንገድ ላይ የተመሰረተ የመጀመሪያው ፓርቲ ሳይሆን አይቀርም:: ጉባዔው ለፓርቲው አሁን የያዘውን መጠሪያ ስም ያወጣ ሲሆን እስክንድር ነጋን ሊቀመንበሩ አድርጎ መርጧል:: ባልደራስ ወደ ፖለቲካ ፓርቲነት እንዲቀየር በአሜሪካና በአውሮፓ የተደረጉ ሕዝባዊ ውይይቶችም በጎ ግፊት አድርገዋል::

## ፓርቲው ምን ሠራ?

ባልደራስ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ እንደመጣ እንደ ሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ በቢሮና በአዳራሽ ፖለቲካ ብቻ አልተወሰነም:: ተጎጂዎች ባሉበት ሁሉ እየሄደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ አደረገ:: የዜጎች መኖሪያ ቤቶች በማንነታቸው ምክንያ ተለይተው በግፍ ሲፈርሱ ፈጥኖ በመድረስ የእሮሯቸው ተካፋይ ሆኗል:: መንግሥት ዜጎችን ከማፈናቀል እንዲቆጠብም አሳስቧል:: የሕዝቡን ፖለቲካዊ ህሊና በእጅጉ ጨመረው:: አዲስ አበባን ብሎም ሀገሪቱን አፍርሶ እንደገና በራስ ቀለም ለመሥራት በሚደረገው ጥረት ቀድሞ የጉዳቱ ሰለባ የሆኑት የአዲስ አበባ ቅርሶችና ታሪካዊ ቦታዎች ናቸው:: በዚህ ቅርሶች እንዳይፈርሱ ባልደራስ ሰፊ ጥረት አድርጓል:: ከፈረሳ ከታደጋቸው ታሪካዊ ቅርሶች መካከልም ለገሀር የሚገኘው የይሁዳ አንበሳ ሀውልት እና በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሲኒማ ቤት ይጠቀሳሉ:: እነኝህ ባልደራስ ሕዝቡን በማንቃት በተቃውሞ እንቅስቃሴ ስለጀመረ በታቀደው መሰረት ሳይፈርሱ የቀሩ ናቸው:: በፈረሱ ቅርሶች ላይም ተቃውሞዎችን በማሰማት ላይ ይገኛል:: የሀገረ መንግሥቱ ምልክት የሆነው እና ከኢትዮጵያውያን ስነ ልቦና ጋር እጅግ የተቆራኘው የይሁዳ አንበሳ ቤተመንግሥቱ ግቢ ላይ ‹ፒኮክ› በተሰኘች ወፍ መተካቱንም ባልደራስ ከመቃወም አልፎ ወደ ነበረበት እንዲመለስ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቃውሞ ፊርማ በማሰባሰብ ላይ ይገኛል:: የገዥውን ፓርቲና የመንግሥትን ስህተቶች እየተከታተለ የሚያጋልጠው ባልደራስ በአሁኑ ጊዜ እንቅስቃሴዎቹን ከመገደብም ባለፈ ሊቀ መንበሩን አቶ እስክንድር ነጋን ጨምሮ አመራሮቹ፣ አባላቱና ደጋፊዎቹ በእስር ላይ ይገኛሉ:: የገዥውን ፓርቲ የሴራ ፖለቲካ ተከትሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ግድያዎች በተፈጠሩ ቁጥር መንግሥት የባልደራስ አመራሮችን እያሠረ ነው:: ባለፈው አመት የተፈጠረውን የመንግሥት ባለሥልጣናት ግድያ ተከትሎ በርካታ ተጠርጣሪዎች ሲታሠሩ የፓርቲው አደረጃጀት ጉዳዮች ሓላፊው አቶ ስንታየሁ ቸኮል ለሰባት ወራት ታስረው ቆይተዋል:: በኋላም ወንጀለኛ የሚያስብላቸው አንዳች መረጃ ባለመገኘቱ በነፃ ተሰናብተዋል:: በቅርቡ የአርቲስትና አክቲቪስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎም የፓርቲው አመራሮች ያለ ወንጀላቸው ታስረዋል:: አቶ ስንታየሁ በድጋሜ አሁንም በእስር ላይ ሲሆኑ አቶ እስክንድር ነጋ፣ አስቴር ሥዩም፣ አስካለ ደምሌ እና ሌሎችም አመራሮች በእስር ላይ ናቸው:: ችሎቱ በመጋረጃ የተከለሉ ምስክሮች የተሰሙበት መሆኑ ደግሞ አስገራሚ ሆኗል:: ምስክሮቹ አቶ ስንታየሁ ቸኮል በእስር ላይ በነበሩበት ወቅት ‹ከተማ ውስጥ ሁከት ሲፈጥሩ አይቻለሁ› ማለታቸውም መጋረጃውን ገላልጦ የምስክሮቹን ማንነት ያሳየ ተግባር ሆኗል:: በእንዲህ አይነቱ ችሎት ላለመዳኘት አመራሮቻችን በአሁኑ ጊዜ ራሳቸውን ከፍርድ ሂደቱ አግልለዋል:: ጠበቆቻቸውንም አሰናብተዋል:: ሆኖም ወንጀለኛው ፍርድ ቤት በፖሊስ አስደግዶ እያቀረባቸው ይገኛል:: አቶ ስታየሁ ቸኮል በእስር ላይ በሚገኙበት የፌዴራል ፖሊስ የተደራጁ ወንጀሎች ምርመራ ክፍል ውስጥ ለኩላሊት ህመም ተዳርገዋል:: ከብዙ ጉትጎታ በኋላ በፖሊስ ሆስፒታል የታከሙ ቢሆንም አሁንም ጤንነታቸው ስጋት ውስጥ ነው:: በተመሳሳይ ወይዘሮ አስቴር ስዩም በሚገኙበት አዲስ አበባ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ለህመም ተዳርገዋል::

ባልደራስ አዲስ አበባ ራሷን የቻለች ራስ ገዝ አስተዳድር እንድትሆንም የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ ጀምሯል:: ፓርቲው የኢሕአዴግን የፌዴራል አወቃቀር ባይቀበለውም ከተማዋ የገጠር መሬቷ ይመለስ ዘንድ፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውክልና ይኖራት ዘንድ ብሎም በራሳቸው በአዲስ አበቤዎች ትመራ ዘንድ ከዘጠኙ ‹ክልሎች› ትይዩ አወቃቀር ይኖራት ዘንድ እየሠራ ነው::

ባልደራስ በአዲስ በአበባ የሚንቀሳቀስ ‹ክልላዊ› ፓርቲ ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ መወዳደር ያስችለው ዘንድ ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል:: በተጨማሪም ከድሬዳዋ ነዋሪዎች አንድነት ፓርቲ ጋር በትብብር ለመሥራት በዝግጅት ላይ ነው:: በዚህም ቻርተር ከተሞች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራበትን እንቅስቃሴ ያጠናክራል::

የባለሙያዎች የባለአደራ መንግሥት እንዲቋቋም የጠየቀ ሲሆን እንዴት እንደሚቋቋምም የተጠናቀረ ሰነድ አደራጅቷል:: ባልደራስ ባቀረበው ሃሳብ መሰረት ወደ ተግባር ተገብቶ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የተፈጠረው የዘር ፍጅት ላይከሰት ይችል ነበር:: የሀገሪቱ ችግሮችም እንዲህ ተውሰብስበው ባልቀጠሉ ነበር::

በአጠቃላይ ፓርቲው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን እንዳያደርግ እየተከለከለም ቢሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል:: ገዥውን ፓርቲ በፅኑ የሚቃወም ብቻ ሳይሆን የሚገራ ጭምር ሆኖ ቀጥሏል:: ገዥው ፓርቲ በመጭው ምርጫ አዲስ አበባ ላይ አንድም ወንበር እንዳያገኝ ለማድረግም እየሠራ ይገኛል::



# ከታሪክ ሽሚያ እስከ ወረራ

የጠቅላይ ሚንስትር አብይ አሕመድ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ ‹አዲስ አበባ› የሚለው ስያሜ ገሸሽ እየተደረገ ይመስላል። በኦሕዴድ/ኢሕአዴግ መንግሥት እና በኦሮሞ የፅንፈኛ ፖለቲከኞች ሁሉ ስያሜ ከብርሃን ዘ ኢትዮጵያ እቴጌ ጣይቱ እና ከባለቤታቸው ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ጋር ተያይዞ በጥላቻ እየተገፋ ይገኛል። በጠቅላይ ሚንስትሩ የሚመራው የአዲስ አበባ የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎችን ማስዋብ ፕሮጀክት አዲስ አበባ ከሚለው ስያሜ ይልቅ ‹ሸገርን ማስዋብ› በሚል እየተጠራ ነው። በከተማው አስተዳድር የሚመራው የ‹ሸገር ዳቦ› ፕሮጀክትና የ‹ሸገር ዘይት› ፕሮጀክትም ይጠቀሳሉ። የአዲስ አበባ ብዙሃን መገናኛ ድርጅትን ‹ሸገር ሚዲያ ኔትወርክ› ወደ ሚል ስያሜ ለመቀየር ታስቦ እንደነበርም ከድርጅቱ የውስጥ ምንጮች የወጡ መረጃዎች ያመላክታሉ። በተቋሙ ጋዜጠኞችና ሌሎች ሰራተኞች ተቃውሞ ይሄኛው ስያሜ ቀርቶ ‹አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ› ወደ ሚል መቀየሩም ግልፅ ነው። ሸገር የሚባል ከተማ በሕግ አይታወቅም። ከተማችን በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምትታወቀው አዲስ አበባ በሚል ነው። ታዲያ ጠቅላይ ሚንስትሩ ይህንን ስያሜ ከየት አመጡት? ሸገር ምን ማለት ነው?

ዶክተር ሐብታሙ ተገኝ ‹በራራ-ቀዳሚት አዲስ አበባ› በተሰኘው ጥናታዊ መፅሐፋቸው ሸገር፤ ሸጋ አገር ማለት ነው ይላሉ። መፅሐፉ በማጣቀሻነት የተጠቀመው ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ሸዋ ይኖር የነበረው ፈረንሳያዊ ነጋዴ መፍሐፍ ነው። ፈረንሳያዊው ዡል ቦሬሊ ይባላል። በ1880ዎቹ በአዲሱ እንጦጦ ለሦስት ዓመታት ኖሯል። እንጦጦን አማራዎች ሸገር ጨነቅ ይሉት እንደነበር ፅፏል። እንደ ዶክተር ሐብታሙ ጥናት ይህ ሸገር ስለተባለው የቦታ ስያሜ በፅሁፍ የተገኘ የመጀመሪያው ሰነድ ነው። ይሁን እንጂ ዡል ቦሬሊ ሸገር ጨነቅ ስለተባለው ቃል ትርጓሜ አልሰጠም። በአማርኛ የስርዎ ቃላት ትንታኔ ‹ሸገር› ሥር መሰረቱ ‹ሠገረ› ነው። የፅንሰ ሃሳቡ ትርጓሜም በመነሻና በመድረሻ መካከል ያለን ቦታ ማለፍን ወይም መዝነቅን የሚገልፅ ሆኖ እናገኘዋለን። ‹ጨነቅ› የሚለው ቃል መጨናነቅ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህም በደስታ ተክለወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት መሰረት መጠጋጋት ወይም መቀራረብ ከሚለው ትርጓሜ ጋር የተቆራኘ ነው።

ዳግማዊ ምኒልክ በእንጦጦ ሲከትሙ ቀደምት ነገስታት የነበሩበት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በመሆኑም ዳዋ ለብሶ የነበረውን አካባቢ እንደ አዲስ በማደራጀት ሰዎች እንዲሰፍሩበት አድርገዋል። በዚህ ወቅት ምድረ በዳ የነበረው አካባቢ ላይ ሰዎች ተጠጋግተው መኖር ጀመሩ። በመሆኑም ሰዎች አካባቢውን ሸገር ጨነቅ አሉት የሚል ነው እውነተኛ የታሪክ ትንታኔው።

በሌላ በኩል የማሕበረሰብ የቃላት ፍች ትንታኔ (folk etymology) የቃሉን አመጣጥ ከሌላ ማዕዘን ሊያመላክት እንደሚችል ከላይ የተጠቀሰው መፅሐፍ ያብራራል። ለአብነትም ከ‹እግዜአብሔር› እግዚሔር፣ ‹ከደጅ አዝማች› ደጃማች/ደጃች የተሰኙ ቃላት በማሳጠር እንደተፈጠሩት ሁሉ ‹ሸገርም› ሸጋ አገር ከሚለው ሀረግ የመጣ እንደሆነ ይተነትናል።

ከታሪካዊ ማስረጃው መረዳት የሚቻለው ሸገር ይባል የነበረው እንጦጦና አካባቢው ማለትም ዛሬ ድል በር እየተባለ የሚጠራው አካባቢ መሆኑን ነው። ከዚህ ውጭ ሸገር የሚባል ከተማ አልፎ አልፎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአራዳ ቋንቋ ተደርጎ መጠቀሱ ውጭ አይታወቅም። ይሁን እንጂ ስያሜውን እንደ ኦሮምኛ ቃል የሚረዱት የኦሮሞ ፅንፈኛ ፖለቲከኞችም አሉ። ጠቅላይ ሚንስተር አብይ አሕመድ ከፕሮቶኮል ውጭ በሆነ መንገድ ይህንን በሕግም ሆነ በታሪክ እውቅና የሌለውን ስያሜ ለምን እንደሚጠቀሙ ግልፅ አይደለም። ‹ሸገርን ማስዋብ› ላሉት ፕሮጀክት ከ2.9 ቢሊዮን ብር በላይ ወጭ እንደሚደረግም ይፋ አድርገዋል። እንዲህ ጎሰም ያለ ገንዘብ የሚወጣበት ፕሮጅክት እንኳንስ ስያሜው ሌሎች ዝርዝር ነገሮችም በማያሻማ መልኩ መጠቀስ ይገባቸው ነበር። በመሆኑም ጉዳዩን አቶ ሽመልስ አብዲሳ የተናገሩት የማደናገሩ ፕሮጀክት አንዱ ክፍል አድርገን ልንወስደው እንገደዳለን።

ሌላኛው የታሪክ ሽሚያውና የወረራው መነሻ አዲስ አበባን ‹ፊንፊኔ› እያሉ የመጥራቱ አባዜ ነው። ይህም ከአማርኛ እና ከአማራ ለማራቅ የሚደረግ

ጥረት ሲሆን በተመሳሳይ ቃሉ የኦሮምኛ ፍች ያለው መስሏቸው በስህተት የዋጡት የኦሮሞ ብሔርተኞች በርካታ ናቸው። ዛሬ የኦሮሞ ብሔርተኝነት አቀንቃኞችን የሚከተለው ጨዋው የኦሮሞ ሕዝብ እውነት መስሎት እየተቀበለው ነው። የታሪክም ሆነ የቋንቋ ሀቆች የሚያሳዩት ግን የአማርኛ ቃል መሆኑን ነው። እርሱም ከቤተመግሥቱ ግርጌ የሚገኘው እና ፍል ውሃ የተባለው መንደር ብቻ የሚወክል እንጂ አዲስ አበባን ከኬንተሪ እስከ ጣፎ፣ ከድል በር እስከ ኢቃቂ የሚወክል አይደለም።

‹ፊንፊኔ› የሚባለው እስከ ብዙ ዘመን ድረስ የአቦ ጠበል ሲባል የቆየ ነው። እንደ ዛሬው ፍል ውሃ ለሚጠቀመው ሕዝብ መከላከያና መጠለያ ቤት የሌለው ስለነበረ ውሃው ወደ ላይ ፊን ፊን ሲል ይታይ ነበር። ስያሜውን ብርሃን ዘ ኢትዮጵያ እቴጌ ጣይቱ የሰጡት ከዚህ እሳቤ እንደሆነ ታሪክ ያወሳል። ቃሉ መሰረት ወይም ስርዎ ቃል ‹ፊነ› የሚል የሚል ነው። ቃሉ አማርኛ ቋንቋ ከተፈጠረ ጀምሮ የነበረ እንደነበረም ሊቃውንት ያትታሉ። ቆየት ያሉ የአማርኛ መዝገበ ቃላትም ከላይ የተጠቀሰውን ትርጓሜ ሰጥተውታል። ለምሳሌ የከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ‹ፊንፊኔ› የሚለውን ቃል «ፊን ፊን አለ፣ ውሃ ከመሬት ሲመነጭ ወደ አየር ፊን እያለ ከመሬት ላይ ዘነበ» በማለት ተርጉሞታል። ደስታ ተክለ ወልድ እና ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ደግሞ በተመሳሳይ ‹ፊን ፊን አለ፣ ፊን አደረገ ፊነነ› ብለው ተርጉመውታል። በቅርቡ የታተመው የቶማስ ኬን የአማርኛ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ደስታ ተክለ ወልድ እና ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ከሰጡት ትርጓሜ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሌሎች የአማርኛ መዝገበ ቃላትም ይህንኑ ፍች በተመሳሳይ አፅንተውታል።

በአንፃሩ በኦሮምኛ መዝገበ ቃላት ‹ፊንፊኔ› የሚል ቃል አይገኝም። የቦታ ስም ከሆነ በኋላም በኦሮምኛ መዝገበ ቃላት ሰፍሮ አይገኝም። ለምሳሌ ኢ. ሲ. ፉት በፃፈው የኦሮምኛ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ ‹ፊንፊኔ› የሚል ቃል አይገኝም። ዮህንስ ክራፕፍ በፃፈው የኦሮምኛ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ላይም በተመሳሳይ ቃሉ አይገኝም። ይህ ሰው ፍል ውሃ ድረስ ሄዶ ቦታውንም አይቷል። ስለዚህ ቃሉ በቋንቋው ውስጥ ቢገኝ ኖሮ ከዚህ ፀሐፊ መዝገበ ቃላት ውስጥ ሊገኝ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ‹ፊንፊኔ› የኦሮምኛ ቃል ቢሆን ኖሮ ከዮሀንስ ክራፕፍ መዝገበ ቃላት ሊያመልጥ እንደማመይችል በራራ- ቀዳሚት አዲስ አበባ የተሰኘው መፅሐፍ ተንትኗል።

ከተዘረዘሩት በተጨማሪ በ1945 ዓ.ም. ሎውሮንስ ቱሽክ ያሳተመው የኦሮምኛ መዝገበ ቃላት፣ የካቶሊክ ወንጌላዊው እንድሪያስ ጃሮሶ በ1939 ዓ.ም. እንዲሁም በ2004 ዓ.ም. ጥላሁን ገምታ ባሳተመው የኦሮምኛ - እንግሊዝ መዝገበ ቃላት ላይም ቃሉ አይገኝም።

በመሆኑም ‹ሸገር›ም ሆነ ‹ፊንፊኔ› የተባሉት ስሞች ሕጋዊ መሰረት የላቸውም። በኦሮምኛ ቋንቋ ውስጥም አይገኙም። ይልቁንም በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የማያሻማ እና ወጥ ትርጉም አላቸው። ይህ የተሳሳተ የታሪክ ትርክት ሁለቱን ቋንቋዎች በቅርበት ለሚያውቅ ሰው ይበልጥ ግልፅ እየሆነ የሚመጣ ሀቅ ነው። አዲሱ የቁቤ ትውልድም ይህንን ሀቅ መረዳት ይጠበቅበታል።

ይህንን የታሪክ ሽሚያ ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ ከተማዋን ለመውረር፤ መውረር ካልቻለም ለማጥፋት እየተጠቀመበት እንደሆነ ደግሞ የአቶ ሽመልስ ንግግር የማያሻማ ምስክር ነው። የከተማዋን የሕዝብ ስብጥር መቀየሩ፣ ለኑሮም ሆነ ለሥራ የማትመች ማለትም የማትረባ ከተማ ማድረጉም ከላይ ከተገለፀው ማደናገሪያ ጋር የሚዳበሉ ናቸው። የአዲስ አበባን ብሎም የኢትዮጵያን ቅርሶች እየመረጡ ማጥፋቱም የዚሁ አካል ነው ማለት ይቻላል።

## የፈረሱ ቅርሶች

የአዲስ አበባ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ በ2003 ዓ.ም. እና በ2009 ዓ.ም ባደረገው ጥናት መሰረት በአዲስ አበባ ውስጥ በከተማዋ መሪ ፕላን የተካተቱ 440 በቅርስነት የተመዘገቡ ታሪካዊ ቤቶችና ሕዝባዊ ተቋማት አሉ። 33 አብያተ ክርስቲያናት፣ 2 መስጊዶች፣ 1 ታሪካዊ ድልድይ እና 10 ታሪካዊ ሀውልቶችም በከተማዋ ውስጥ ይገኛሉ። በቅርስነት ተመዝግበው በመሪ ፕላኑ ውስጥ ያልተካተቱ ደግሞ 135 ጥንታዊ ቤቶች አሉ። ይህ ሕወሓት/ኢህአዴግ ለራሱ አገዛዝ እንዲመቸው አድርጎ ያስጠናው ሲሆን የቅርሶች ቁጥር ከዚህም በላይ ከፍ እንደሚል ይገመታል። ታዲያ ከእነዚህ ቅርሶች መካከል ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ከፊሎቹን መንግሥት አፍርሷቸዋል። ለአብነትም አድዋ ድልድይ አካባቢ የሚገኘው የራስ አበባ አረጋይ ቤት ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ተደርጓል። ከዘጠና ዓመት በላይ ያስቆጠረው የልዑል ራስ ካሳ ልጅ የፊታውራሪ አምዴ አበራ መኖሪያ ቤት በከፊል ፈርሷል። ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ፣ የአካባቢው ነዋሪዎችና ሌሎችም ለመከላከል ባደረጉት ጥረት በከፊል ተርፏል። የፊደል ገበታ አዘጋጅ የተሰፋ ገብረ ስላሴ ዘብሔረ ቡልጋ መኖሪያ ቤትና ማተሚያ ቤት የነበረውም ከፈረሱት መካከል ይጠቀሳል። ይህ ቤት ከመቶ አመታት በላይ አስቆጥሯል። የለገሀሩ ቡፌ ዲላገር ፈርሷል። ኤግል ሂልስ ለተባለ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ኩባንያ ሕንፃ እንዲገነባበት ያለጨረታ ተሰጥቷል። ይህ ጠቅላይ ሚንስትሩ ራሳቸው ሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተጫራቾችን አግልለው ለአረብ ወዳጆቻቸው የሰጡት ነው። አዲስ አበባ የሚገኘውን ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ለማፍረስ ቢሞክርም ለጊዜው በሕዝብ ተቃውሞ ተርፏል። ሰይጣን ቤት የተባለው የመጀመሪያው ሲኒማ ቤትም እንዲሁ በባልደራስ እና በሌሎች አካላት ጥረት ከመፍረስ ተርፏል። የእቴጌ ጣይቱ ብጡል ብርሐን ዘ ኢትዮጵያ መታሰቢያ ሀውልት በቆረቆሯት ከተማ አዲስ አበባ ላይ እንዳይሠራ ተከልክሏል። ሐረር ከተማ ውስጥ ከሁለት ወራት በፊት የራስ መኮንን ሐውልት ፈርሷል። ከዚህ ቀደም ብሎ ደግሞ ጎሬ ከተማ አደባባይ ላይ የአቡነ ሚካኤል ሀውልት እንዳይቆም ተከልክሏል። ይህ ሐውልት ከተማዋን ከሁለት ከፍሎ ወደ መቱ እና ወደ ጋምቤላ የሚያልፈው አውራ ጎዳና አደባባይ ላይ እንዲቆም ነበር በከተማዋ ኗሪዎች የታሰበው። ሆኖም የወቅቱ የኦሕዴግ ካድሬዎች በመከልከላቸው ለከተማዋ የታሰበው የመታሰቢያ ሀውልታቸው በእዚያው በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲቆም ተደርጓል። አቡነ ሚካኤል የጣሊያን ወራሪ ኃይል በኢልባቡር በኩል ለመግባት ሲሞክር ፊት ለፊት ተዋግተው ሳምቤ ላይ ድል ያደረጉ የኃይማኖት መሪ ነበሩ። ታሪካቸው እምብዛም ጎልቶ ባይታወቅም እንደ አቡነ ጴጥሮስ ሁሉ ባዕዳን ወራሪዎችን ያሳፈሩ ቆራጥ አባት ናቸው። አካባቢውን ከሌሎች አርበኞች ጋር በመሆን ከወራሪ ታድገው ሀገር ከእነ ክብሯ አስቀጠሉ። እሳቸው ባስቀጠሏት ሀገር የኦሕዴግ ካድሬዎችም ባለሥልጣን፤ አዛዥ ሆኑ። ከአመታት በኋላ ግን የእሳቸውን ታሪክ ከመዘከርና ከማመስገን ይልቅ ዘር ቆጥረው ሃውልታቸው እንዳይቆም ከለከሉ። የአቡነ ሚካኤል ሀውልት በቦታው እንዳይቆም ዋነኛው ምክንያታቸው አማራና አርቶዶክስ ተዋህዶ ጠልነታቸው ነው። አቡኑ ጎንደር፤ ደብረ ታቦር ነው የተወለዱት። አማራ ነኝ ብለው ግን የኢልባቡርን ሕዝብ ለወራሪ አሳልፈው አልሰጡም፤ ፊት ለፊት ተጋፍጠው ከመገዛት አዳኑት እንጂ፤

በወቅቱ በአማራና በኦሮሚያ በኩል ጠንካራ ሕዝባዊ አመፆች ይነሱበት የነበረው ኢሕአዴግ ማለትም ሕወሓት ኢሕአዴግ መሰል ጥፋቶችን ያቀነባብር እንደነበርም በግልፅ የሚታይ ሀቅ ነው። በተለይም የብአዴን እና የኦሕዴድ አመራሮች የውስጥ ለውስጥ ስውር ትግል ያደርጉበት እንደነበር ሲያውቅ ይህንን እንደ ማስፈራሪያም በግልፅ ይናገረው ነበር። በ2003 ዓ.ም ባስጠናው ጥናት መሰረት በቅርስነት የዘረዘራቸውን ታሪካዊ ቤቶች፣ድልድዮች እና ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ የኦሮምኛ ስም እየሰጠ ሊቀይራቸው እንደሚችልም በመግለጫ አስፈራርቷል። ይህ የሕወሓት መግለጫ ከማስፈራሪያነት በዘለለ እውን ሊሆን እንደሚችልም መገመት ይቻላል። ምክንያቱም የሥልጣን ጊዜውን ለማራዘም ሲል በዙሪያው ያሉትን ሁሉ እርስ በእርስ ማጋጨት ቀዳሚ ተግባሩ ነው። ምክንያቱም የአኖሌ ሀውልትን ገንብቷል። ምክንያቱም የኦሮሚያ ‹ክልል›ን ዋና ከተማ ከናዝሬት አንስቶ ወደ አዲስ አበባ ቀይሯል።

# ስር የሰደደው የዐቢይ የተቋም አተካከልና ክትትል ችግር



**ገለታው ዘለቀ**

**(የባልደራስ ፅህፈት ቤትና ሕዝብ ግንኙነት ሓላፊ)**



ከሁለት አመታት በፊት በሃገራችን የፖለቲካ ለውጥ የሸተተን መስሎን ስለ ሽግግር ብዙ አልን፤ እጅግ በጣም ጥቂት ሰዎች ለውጡ መጣሁ መጣሁ ሲል በፍጥነት የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አለብን የሚል ድምጽ አሰሙ:: ይህ ድምጽ ግን በጣም የጥቂቶች ነበር:: አብላጫው ሰው ዶ/ር አብይ የሚመሩት መንግሥት የሽግግሩን ሥራ ይስራው የሚል ነበር:: ለለውጡ በጣም የሳሱ ኢትዮጵያውያን ምሁራን የዶ/ር አብይን መንግሥት በርታ፣ ጎበዝ፣ እሰየው----- ካልነው እየገፋ ይሄዳል የሚል ሳይንስ የጎደለው ዝንባሌ አሳይተዋል:: ያለ ሽግግር መንግሥት ኢትዮጵያ ወደ ተፈላጊ ለውጥ ልታልፍ አትችልም:: ስለዚህ በአስቸኳይ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የሚለው ቀጭን ድምጽ ከዚህም ከዚያም ዱላ በዛበት:: የሽግግር መንግሥት አያስፈልግም በዚህ የለውጥ ኃይል ላይ ሌሎች ለሽግግሩ የሚያግዙ ተቋማት ከተገነቡ እነዚህን ተቋማት ይዞና ክፍተቱን ሞልቶ የለውጡ ኃይል ራሱ ሽግግሩን ይመራዋል ተባለ:: ብዙ ሰው ለለውጥ ስለጓጓና የህወሃት ዘወር ማለት ስላስደሰተው ጠንከር ብሎ ሳይመራመርና ሳይጠይቅ ለዶ/ር አብይ ዲስኩሮች ጭብጨባውን አቀለጠው:: እኚህ ሰው ወደ ስልጣን ሲመጡ የለውጥ ኃይል በራሱ ሽግግር ለመምራት ምሉዕ የመሆን ተፈጥሮ ስለማይኖረው ለሽግግሩ አጋዥ የሆኑ ተቋማትን መፍጠሩ ነገር በጉጉት ተጠበቀ::

ታዲያ ሲጠበቁ የቆዩት ጠቅላይ ሚ/ር ከሚጠበቁት ተቋማት መካከል የብሔራዊ እርቀ ሰላም ኮሚሽንና የማንነት፣ የአስተዳደርና ወሰን ጉዳይ ኮሚሽንን አቋቋሙ:: “ጠቅላይ ሚኒስትሩ” እነዚህን ተቋማት ሲተክሉ የነበሩትን ችግሮች በመዘርዘር የእኚህን ሰው የሲስተምና የተቋም አገነባብ ችግር እስቲ ዛሬ እንወያይበት፡

### 1.ሲስተምና ሚኒስትሪ

የዶ/ር አብይን የተቋም አተካከል መሠረታዊ ችግር ያየሁትና የፍልስፍና ችግሮቻቸውን የተማርኩት የሰላም ሚንስቴር የሚባል የሚንስቴር መስሪያ ቤት ሲመሰርቱ ነው:: ይህ ተቋም ሲመሰረት የመጀመሪያው ጉዳይ “ሰላም” የሚባለውን ጽንሰ ሃሳብ የተረዱበት መንገድ ነው የገረመኝ:: ሰላም እውነት ነው ለአንድ ማህበር / ሃገራዊ ሕብረት / እጅግ ወሳኝ የሆነ መተሳሰሪያ መርሆ ነው:: ሰላም ብቻ አይደለም ነገር ግን ፍቅር፣ በጎነት፣ መተሳሰብ፣ የመሳሰሉት ረቂቅ በጎ ነገሮች ሁሉ ለሕብረተሰባችን እጅግ አስፈላጊ መተሳሰሪያ መርሆዎች ናቸው:: ሀብታም ሆነን ነገር ግን ሰላም ባይኖረን ሃብታችን ምን ይፈይዳል? ምን ዋጋ አለው? ሁሉ ኖረን ፍቅር ግን ቢጎድለንና በብሔሮች መካከል ወይም በዜጎች መካከል መተማመን ቢጠፋ ፍቅራችን ቢተንብን ሃብታችን ከቶ ምን ይጠቅመናል? እውነት ነው ሰላም ፣ ፍቅር፣ በጎነት፣መተማመን፣መረዳዳት እና ሌሎች አስፈላጊ መርሆዎች ሁሉ የህብረታችን እጅግ አስፈላጊ የመተሳሰሪያ መርሆዎች ናቸው።

ይሁን እንጂ እነዚህ መተሳሰሪያ መርሆዎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የምናቋቁምላቸው አይደሉም። የፍቅር ሚንስቴር፣ የበጎነት ሚኒስቴር፣ የሰላም ሚንስቴር፣ ወዘተ እያልን መንግሥታዊ ተቋም አንመሰርትላቸውም። ለምን ቢባል እነዚህ ‹ኤለመንቶች› በተፈጥሮ አንድ ገዢ ፓርቲ የሚመራቸውና የአንድ አካል ውጤት አይደሉም። የብዙ ተቋማት፣ የሃይማኖትና የባህል ውጤቶች ናቸው እንጂ በተፈጥሯቸው የመንግሥት ተቋማት አይደሉም:: ነፃ ተቋማት ናቸው:: መንግሥት ሰላምን ፖለቲካዊ ሊያደርገው አይችልም:: ሰላም በተፈጥሮው ገለልተኛነትን፣ ነፃነትን ይጠይቃል:: መንግሥት ከአንድ ሃገራዊ ኃይል ጋር ቢጋጭ የሰላም ሚኒስቴር ጣልቃ ገብቶ የመካከለኛነት ሚና ሊጫወት አይችልም:: የዶ/ር አብይ ፍልስፍና ችግር ይህ ነው:: ሰላምን ፖለቲካዊ በማድረጋቸው ሠላምን ጎድተዋል፤ ተቋሙን ጎድተዋል:: በሀገራችን ሊመሠረቱ የሚችሉ የሰላም ገለልተኛ ተቋማት እንዳይፈጠሩ አሉታዊ ሚና ተጫውተዋል::

ሁለተኛው የዚህ የሰላም ሚኒስቴር ተቋም ችግር ይዘቱ ነው:: በሰላም ሚኒስቴር ስር ያሉት ተቋማት ከዚያም ከዚህም የተሰበሰቡ ተቋማት ናቸው:: እነዚህን ሁሉ በአንድ ቋት ውስጥ አስገብቶ የሰላም ሚኒስቴር ማለት እውቀት የጎደለው ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ የሚጋጩ ሁኔታዎችን ያመጣል:: ስለ ሰላም ስናስብ ትምህርት፣ ፖሊስ፣ ወታደር ሁሉም በአንድም በሌላም መንገድ ለሰላም አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ ይታሰባል:: ነገር ግን እኚህ ሰው ከተቋማቱ የተወሰነውን መርጠው ለሰላም የቀረበ ሌላውን ራቅ ያለ አድርገው ማሰባቸው ሌላው የአምክኖት የተቋም አተካከል ችግራቸውን ያሳያል:: ሰላም በገለልተኛ ተቋማት፣ በሃይማኖት፣ በባህል፣ በትምህርት ተቋማት ቢያዝ ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት ሽምግልናን ለማምጣት ያስችላል። ለምሳሌ መንግሥት ከአንድ ኃይል ጋር ቢጣላ የሰላም ሚንስትር ወ/ሮ ሙፈርያት ሽማግሌ ሆነው መቅረብ አይችሉም፤ ለሰላም መካከለኛ

አይሆኑም። ዶክተር አብይ ሰላምን የተረዱበት መንገድ ስህተት ነው።

ለሰላም ሚንስቴር ተጠሪ ከሆኑት ተቋማት አንዳንዶቹ ከዚህ በፊት ለደህንነት መስሪያ ቤቱ ተጠሪ የነበሩ መሆናቸው ይታወቃል። ለአብነትም ፌዴራል ፖሊስ፣ ይጠቀሳል።

የሰላም ሚንስቴር ወደ ‹ክልሎች› እና ከተማ አስተዳደሮች በሚወርድበት ጊዜም በቀጥታ ከደህንነት መስሪያ ቤቱ ጋር የተዳበለ ነው። በ‹ክልል›ና ከተማ አስተዳደር ደረጃ ‹የሰላምና ደህንነት ግንባታ ቢሮ›፣ በዞን/ክፍለ ከተማና ወረዳ አደረጃጀት ደግሞ በዚሁ ስያሜ መምሪያና ፅህፈት ቤት ተብሎ በቅደም ተከተል ይወርዳል። ዛሬ አዲስ አበባ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎችና አቻ ተቋማት የሚሰጧቸውን ጋዜጣዊ መግለጫዎች የሚፈቅደውና የሚከለክለው የሰላም ሚንስቴር ሆኗል። ነገሮች ለመንግሥት ሥልጣን አስጊ መሆን አለመሆናቸውን የሚሰልለው ሀይል በዚሁ በሰላም ሚኒስቴር በኩል ነው። በመሆኑም ሰላም ሚንስቴር ከላይ ሲታይ የአሸማጋይነት ሚና ያለው የሚመስል ስም ተሸክሞ ውስጡ ግን የስለላ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል።

### 2.የአዲስ አበባ የሰላም ም/ቤት

ይህ ተቋም ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የጠቅላይ ሚንስትሩን ፈለግ ተከትለው ከታከለ ኡማ የምክትል ከንቲባነት ሥልጣኑን እንደተቀበሉ ያቋቋሙት ነው። ሥራው በቀጥታ ፀጥታን ከማስከበር ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችልም ገልፀዋል። አዲስ አበባ የራሷ መደበኛ ፖሊስ አላት፣ ‹ተወርዋሪ ኃይል› የሚባል ልዩ የፖሊስ ሰራዊት እንዲሁም ከላይ በተጠቀሰው ተዋረድ መሠረት የሰላምና ደህንነት ግንባታ ቢሮ አላት። አዲሷ ከንቲባ የፈጠሩት ተቋም ተመሳሳይ ሥራ የሚሠራ ሌላ ተቋም ነው። ሰላምን ፖለቲካ የማድረጉን ሥራ በቀጥታ የወሰዱት ከጠቅላይ ሚንስትሩ ነው።

### 3. የማንነትና አስተዳደር ወሰን ኮሚሽን

ሁለተኛው የዶ/ር አብይ የተቋም አተካከል ችግር የሚታየው ደግሞ በማንነት አስተዳደርና ወሰን ኮሚሽን ላይ ነው። ይህ ተቋም ሲተከል ወደ ግማሽ መቶ ሰዎችን የያዘ ሲሆን የተለያዩ የፖለቲካ መሪዎችን ከዚያም ከዚህም አጠራቅመው የተከሉት ተቋም ነው። ከማንነት ጋር፣ ከአስተዳደር ወሰን ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት ገለልተኛ ሆኖ የመፍትሄ ሃሳብ የሚያቀርብ ነው ተብሎ ነበር የታሰበው። ይህ ኮሚሽን ሲቋቋም እኔ እራሴ ደስ ብሎኝ ነበር። ይሁን እንጂ በጽሞና ሳየው ይህንን ኮሚሽን ያቋቋሙት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚያም ከዚህም ተሰባስበው በመሆኑ የውቅር ችግር እንዳለው ያሳያል።

ይህ ኮሚሽን ከአተካከሉ ችግር እንዳለበት ማሳያ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል በኮሚሽኑ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌላቸውን ሁሉ ማካተቱ ነው። ይህ ምን ማለት እንደሆነ አይገባኝም። በአጠቃላይ የማንነት፣ አስተዳደርና ወሰን ኮሚሽን ለኢትዮጵያ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ፣ ሽግግሩን መስመር ለማስያዝ አጋዥ ኮሚሽን ሆኖ ሳለ፣ ነገር ግን የጠ/ሚኒስትሩ ተቋም አመሠራረት ችግር ይሄውና ይህንን ኮሚሽን አንካሳ አድርጎታል። ለሽግግሩ ደራሽ አልሆነም። ባለበት ሳይንቀሳቀስ የሥራ ዘመኑም ሊጠቃለል ነው። በአሁኑ ሰዓት እኚህ ሰው ከዚያም ከዚህም የማይግባቡ ፖለቲከኞችን ሰብስበው አጠራቅመው የመሰረቱት ኮሚሽን በአሁኑ ሰዓት ብዙዎቹ ከኮሚሽኑ ጋር ግንኙነትም የላቸውም። ይህንን አስፈላጊ ኮሚሽን ዶ/ር አብይ ሲተክሉ ስላበላሹት ለሽግግሩ ደራሽ አልሆነም። እኚህ ሰው በአንድ በኩል ይህንን ኮሚሽን አቋቁሙና ደቡብ የማንነት ጥያቄ ተነሳ ሲባል በአባ ዱላ የሚመሩት የማንነት ኮሚቴ መሠረቱ እየተባለ ሲወራ ነበር። እውነት ሆነ ውሸት ሰውየው ግን የተቋም አተካከልና ክትትል መሠረታዊ ችግር እንዳለባቸው በጣም ተምረናል። ይህ ኮሚሽን ነጻ ሆኖ መፈጠር ነበረበት።

### 4. የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን

ኢትዮጵያ ወደ ለውጥ ስትገባ ሽግግሩ የተሻለ እንዲሆን ከሚያስፈልጉት ወሳኝ ተቋማት መካከል የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን ነበር። ይህ ኮሚሽን እንዲቋቋም ብዙ ግፊት ነበር። ዶ/ር አብይ ይህንን ኮሚሽን በፍጥነት አቋቁመው ሽግግሩን እንዲያሳልጡ ሲመከሩ ቆይተዋል። የኮሚሽኑ አስፈላጊነት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለፉ ክፉ ትውስታዎችን ለማጽዳት፣ በካሳ ላይ ያተኮረ ፍትህ በማምጣት ብሔራዊ ፈውስ ማውረድ፣ በመካከለኛነት አገልግሎት ለጠፉ ጥፋቶች ፍትህን ማውረድ፣ የተጣላን ማስታረቅ ነበር። ይሁን እንጂ እኚህ ሰው ይህንን ኮሚሽን ሲያቋቁሙ ወዳጃቸውን የኢዜማ መሪ ዶ/ር ብርሃኑን ጨምረው ሌሎች የፖለቲካ መሪዎችን ሳይቀር ከሃይማኖት መሪዎቹ ጋር አቀላቅለው ፈጥረውታል። ብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን በገለልተኛነት የሚመራ ተቋም ነው። የሽምግልና ቁጥር አንድ መርህ ገለልተኛነት ነው ይባላል። እኚህ ሰው አወላከፈው የፈጠሩት ብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን ሽግግሩን እያገዘ አይደለም። አልፎ አልፎ የተወሰኑ ሰዎች በቴሌቭዥን ብቅ እያሉ አለን ቢሉም ኮሚሽኑ የለም። የማንነት አስተዳደርና ወሰን ኮሚሽንም ሆነ የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን ሽግግሩን ለማገዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ ተብሎ ይጠበቅ ነበር። ይሁን እንጂ ዶ/ር አብይ አወላክፈው ስላቋቋሙት እነሆ ቢሮው ክፍቱን እንዲሁ ይውላል።

### 5. የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ትረስት ፈንድ


ዶክተር አብይ ወደ ስልጣን ሲመጡ በመጀመሪያዎቹ ቀናት ብዙ ሰው ደግፎ ነበር። አብዛኛው ድጋፍ በህወሃት ጥላቻ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ግን ትክክል አልነበረም። የትግላችን ግብ ህወሃትን ገለል ማድረግ ብቻ ሳይሆን መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ነበር። የሆነ ሆኖ ዶክተር አብይ ከሃገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን ድጋፍ ለመሰብሰብ ሞክረው ነበር። ያቺን ጊዜያዊ ተቀባይነት አይተው ይሆናል ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ለሃገራቸው ገንዘብ እንዲያዋጡ አንድ ሃሳብ አመጡ። ይህ ሃሳብ በራሱ መልካም ነበርና ሁላችንም ደግፈናል። ውጭ ሃገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ሃገራቸውን ተደራጅተው ቢረዱ በጣም ተገቢ ነው። እንዴውም እስካሁን ብዙ በዚህ ጉዳይ ላይ አልሠራንምና ብዙ ልንሠራ ይገባል። የዶክተር አብይ ችግር ይህንን ሃሳብ ወደ ተቋም ሲቀይሩ ነው። እንደ ጠቅላይ ሚንስትር ኢትዮጵያውያን ሃገራችሁን ደግፉ የሚል ምክርና ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ነው። ነገር ግን ራሳቸው ቦርድ ሾመው አደራጅ መሆናቸው ግን ከባድ ስህተት ነበር። ይህ ተቋም በተፈጥሮው ነጻ ነው መሆን የነበረበት። ይህ ተቋም በዶክተር አብይ ሹመት የሚመራ ከሆነና ፖለቲካዊ ከሆነ የህዝቡ ድጋፍ ከፖለቲካው ሙቀት ጋር ይዋዥቃል። ለዚህም ነው የዶክተር አብይ ቅቡልነት መውረድ ሲጀምር አንዳንዶች ያዋጡትን ገንዘብ መልሱልኝ እስከማለት የደረሱት። ይህ ተቋም ከፖለቲካ ሹመት ጋር ባይገናኝ ኖሮና ነጻ ቢሆን ሁሉን አቃፊ ስለሚሆን ተቋሙ ያድግ ነበር። የዶክተር አብይ የተቋም አመሠራረት ችግር አንዱ ማሳያ ይህ ነው። ዛሬ ይህ ተቋም ከፍተኛ የቅቡልነትና የማንነት ኪሳራ ውስጥ ገብቷል። ትረስት ፈንድ በአንድ በኩል አሜሪካ ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ ቢሆንም ነገር ግን የዶክተር አብይ ተቋም ሆኖ ያገለግላል። ሲቪክ ድርጅቶች ነጻ መሆን አለባቸው።

### 6. የዶክተር አብይ ርዕይ

ስለተቋም ስናነሳ ተቋም የርዕይ ማስፈጸሚያ አንድ ብርቱ መሳሪያ ነው። የዶክተር አብይ ርዕይ አረንጓዴ አሻራ ነው ይላሉ። መቼስ ልዩ ልዩ ተክሎችን መትከል መናፈሻ መሥራት አስፈላጊ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ለዚህ ጠቅላይ ሚንስትር መሆን አያስፈልግም። ከከንቲባዎች በታች ባለሙያዎች ይህንን ይሠሩታል ያስተባብራሉ። አሁን ኢትዮጵያ የምትሻው ጠቅላይ ሚንስትር ከፍተኛ የሆኑ መዋቅራዊ ለውጦችን ማምጣት፣ ብሄራዊ መግባባትን ማምጣት፣ ሃገሪቱን ለምርጫ ማዘጋጀት፣ መተሳሰሪያ መርሆዎቻችን እንዲሻሻሉ መሥራት፣ የመንግሥት ቅርጾችን ለማሻሻል መሥራት የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመሥራት ነው። ዶክተር አብይ ይህንን ነበር ማለም የነበረባቸው። ነገር ግን የሳቸው ህልም የተለያዩ መናፈሻዎች ሆነው ቀርተዋል። ለውጥ ያስፈልገናል።

# ሕገ ወጡ ሕግ

ገዥው ፓርቲ ውስጥ የተፈጠረን የሥልጣን ሽኩቻ ተከትሎ ሕወሓት ሌሎች እህት ድርጅቶቹን አጣልቶ የራሱን የፖለቲካ ብልጫ ለመውሰድ አንድ አዋጅ አወጀ። ይህም ኦሮሚያ ‹ክልል› አዲስ አበባ ላይ ልዩ ጥቅም አለው ሲል ሕወሓት በሚንስትሮች ምክር ቤት በኩል ከሦስት ዓመታት በፊት ያወጣው መግለጫ ዛሬ በቀጥታ ተፈፃሚ እየሆነ ነው። በመግለጫው ከተካተቱት መካከል በከተማ አስተዳድሩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቋንቋ ኦሮምኛ እንዲሆን ይገልፃል። ይህ በአንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ሲደረግ ታይቷል። አዲስ አበባ፤ ዓለም ገና ውስጥ ያለ ትምህርት ቤትም በአማርኛ አላስተምርም በማለቱ ከወላጆችና ተማሪዎች ጋር ግጭት መፈጠሩ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ከሰሞኑ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚሠሩ ርዕሳነ መምህራን መካከል ማለትም ዋናው ወይም ምክትሉ የኦሮምኛ ቋንቋን በአግባቡ መናገር፣ መስማት፣ መፃፍና ማንበብ እንዲችሉ ያስገድዳል። ይህ የትምህርት አመራሩን በመቆጣጠር ትውልዱን የመቆጣጠር ሥራ ነው። የገዳ ሥዓርት አዲስ አበባ ውስጥ በትምህርት ስርዓቱ ተካቶ ኦሮምኛን በሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ሊሰጥ እንደሆነ መንግሥት ይፋ አድርጓል። ይህም ቀስ በቀስ ከተማዋን ወደ ኦሮሚያ የማጠቃለል እንቅስቃሴ ነው።



በተመሳሳይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ከደረጃቸው ወርደው በመምህርነት ወይም በአስተባባሪነት እንዲቀጥሉ ተደርገዋል። ይህም ከማንነት ተኮር ማፈናቀል ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ነባር ርዕሳነ መምህራን ተማረው ትምህርት ቤቶቹን ለቀው እንዲወጡ የሚገፋፋ ነው።

ሁለተኛው ኦሮምኛ በከተማ አስተዳድሩ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን የሚል ነው። ይህንን በፖሊሲ ደረጃም መደበኛ መዋቅር ይዞ ከመውረዱ በፊት ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አሕመድ እና የቀድሞው ምክትል ከንቲባ ታከለ ኡማ ተግባር ላይ አውለውታል። ሁለቱም በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን የሚያስተላልፏቸውን መልዕክቶች በኦሮምኛና በአማርኛ ይፅፋሉ። መገናኛ ብዙሃንም ይህንን ወስደው በዜና መልክ በድጋሜ በመደበኛ መገናኛ ብዙሃን ያሰራጩታል። ጠቅላይ ሚንስትሩ በሁለቱም ቋንቋዎች የሚፅፉ ሲሆን ታከለ ኡማ ግን በኦሮምኛ ብቻ የሚፅፉበት ጊዜም ብዙ ነበር። ለየትኛው አዲስ አበቤ ይሆን በኦሮምኛ የሚፅፉት? በቅርቡ ስለወጣው የቋንቋ ፖሊሲ ሽመልሽ አብዲሳ የፌዴራል የሥራ ቋንቋዎችን በማብዛት አማርኛን እየገደሉና ኦሮምኛን እያስፋፉ እንደሆነ የተናገሩትን ስንጨምርበት ነገሩን ይበልጥ ግልፅ ያደርገዋል።

ሌላኛው ልዩ ጥቅም የኦሮሞ ማንነትን የሚያንፀባርቁ ባሕላዊ ጉዳዮች በከተማው ይበልጥ እንዲስፋፉ የሚል ነው። እነሆ ከ150 አመታት በኋላ ፖለቲካዊው ኢሬቻ በአዲስ አበባ ተከብሯል፤ ምስጋና ለለውጡ? ሌላው ታላላቅ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች፣ አደባባዮችና ሰፈሮች በኦሮምኛ እንዲሰየሙ የሚል ነው። ኢሬቻ አዲስ አበባ ላይ እንደተከበረ የእያንዳንዱን የአዲስ አበባ ሰፈር የኦሮምኛ ስም አውጥተውለታል። ስያሜውም በቢልቦርድ ተዘጋጅቶ በከተዋ የተለዩ አካቢዎች ሕዝብ እንዲያነበው ተለጥፏል። የኦሮሞ ባንኮች ቅርንጫፎቻቸውን የሚሰይሙት በዚህ መሠረት ነው። አርቲስትና አክቲቪስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ይሄኛውን ልዩ ጥቅም ለማስፈፀም ተጠቅመውበታል። በስሙ ትምህርት ቤቶች፣ ጎዳናዎችና መናፈሻዎች ተሰይመዋል።

የከተማዋ መጠሪያ ‹ፊንፊኔ› እና አዲስ አበባ በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውም ሌላኛው ልዩ ጥቅም ነው። ይህ በጠቅላይ ሚንስተር አብይ መሪነት እየተፈፀመ ነው። ጠቅላይ ሚንስተሩ በአማርኛና በእንግሊዝኛ አዲስ አበባ እያሉ ፅፈው ያቸውን ከተማ መልሰው በኦሮምኛ ሲፅፉ ‹ፊንፊኔ› ይሏታል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሸገር በማለት ሲያደናግሩ ይታያሉ።

በጥቅሉ ይህ አዋጅ ከተማዋን አሳልፎ ለአንድ ወገን የሰጠ ሕገ ወጥ አዋጅ ነው። በአንፃሩ ፅንፈኛ የኦሮሞ ፖለቲከኞች ደግሞ ‹በከተማችን ልዩ ጥቅም ሳይሆን የሙሉ ጥቅም ባለቤቶች ነን› ሲሉ ይደመጣሉ።

# በአርሲ እና ባሌ የተፈፀሙ ጥቃቶች



**በላይ ማናዬ (ካርድ- የመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል)**

*ጋዜጠኛ በላይ ማናዬ ይህንን ዘገባ አጠናቅሮ ለመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) ካደረሰ በኋላ ከሌሎች ሦስት የአማራ ሳተላይት ራዲዮና ቴሌቪዥን(አስራት) ባልደረቦቹ ጋር በተረኛው የኦሕዴድ/ብልፅግና መንግሥት በእስራት ላይ ይገኛል።*

## መግቢያ

ድምፃዊ እና አክቲቪስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ሰኔ 22 ቀን 2012 ምሽት 3፡00 ገደማ በአዲስ አበባ የግድያ ወንጀል ተፈፅሞበታል። በሀጫሉ ላይ የተፈፀመው የግድያ ዜና መሰማቱን ተከትሎ በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች እና በአዲስ አበባ የፀጥታ ችግሮች ተፈጥረዋል፤ ጥቃቶች ተፈፅመዋል። በጥቃቱም የሰዎች ሕይወት አልፏል፤ ንብረትም ወድሟል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የካሕናትና የምዕመናን ኅብረት የፀጥታ ችግሮች በነበሩባቸው አካባቢዎች የሚዲያ እና ሲቪክ ተቋማት ተወካዮችን ያካተተ ጉዞ ከሐምሌ 23-25/2012 ለሦስት ቀናት አድርጓል። እኔም የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) በዚህ ጉዳይ ላይ ለሚያደርገው መረጃ ማሰባሰብ ሥራ ለማበርከት በተወሰኑ ሥፍራዎች በጉዞው ተሳትፌ ያገኘሁትን መረጃ እንደሚከተለው አቀናብሬዋለሁ።

ይህ ዘገባ በተለይ በአርሲ እና ባሌ አካባቢዎች የነበረውን ሁኔታ የሚያሳይ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች በተለይም፣ በአርሲ ዴራ፣ አሰላ፣ ገደብ አሳሳ፣ ሮቤ፣ ጎባ እና አጋርፋ የደረሰውን ጉዳት መመልከት ችያለሁ። በነበረው ችግርም ሃይማኖትን እና ብሔርን የለዩ ግድያ፣ ዘረፋ እና ቃጠሎ መፈፀሙን ተረድቻለሁ። ጥቃቱ በሚፈፀምበት ወቅት ፖሊስ "ትዕዛዝ አልተሰጠኝም" በሚል ለሰዓታት ሁኔታውን በዝምታ መመልከቱንም ከዓይን እማኞች ሰምቻለሁ። በአንዳንድ ሥፍራዎች አሁንም የፀጥታ ስጋቱ አለ። በዚህ የተነሳም በተለይ፣ በአርሲ ዴራ፣ በገደብ አሳሳ እና አጋርፋ በርካቶች በቤተክርስቲያናት እና በትምህርት ቤቶች ተጠልለው ይገኛሉ። መንግሥት ስጋታቸውን ለመቅረፍ እያደረገ ያለው ጥረት በቂ አለመሆኑንም ገልጸዋል።

## አርሲ፤ ዴራ

በዴራ ከተማ አስተዳደር ግድያ፣ ዘረፋ እና ቃጠሎ ተፈፅሟል። በጥቃቱ ማግስት በከተማዋ በሚገኘው መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን እስከ 400 በላይ ሰዎች ተጠልለው የነበረ ሲሆን፣ አሁን ላይ (ከአንድ ወር በኋላ መሆኑ ነው) ቁጥራቸው ቀንሷል። አንዳንዶች ከአካባቢው ለቅቀው ወጥተዋል። ሆኖም፣ አሁንም በቤተክርስቲያኑ ተጠልለው የሚገኙት ሰዎች ከ150 በላይ እንደሚሆኑ የደብሩ አስተዳዳሪ ገልጸዋል። በዴራ ሰኔ 22 ቀን 2012 ለ23 ዕኩለ ሌሊት ጀምሮ በተፈፀመው ጥቃት 4 ሰዎች ተገድለዋል። ሆቴሎችና መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል፤ ዝርፊያም ተፈጽሟል። ችግሩ በጥይት ተኩስ እና በጩኸት የተጀመረ ነበር።

"ሀጫሉ ሞቷል እንደተባለ በከተማው ጩኸት ነበር። በሰዓቱ ጩኸቱን ሰምቶ ከቤቱ የወጣ ሰው ብዙ ነበር። ትንሽ ቆይተው እኛም እንገድላለን እያሉ የሚዝቱ ወጣቶች ተሰባሰቡ። ቀጥሎ ከተማዋ በተኩስ ተናጠች። ፖሊስና መከላከያ የደረሰልን መስሎን ነበር። ለካ ወጣቶች ከገጠርም በመኪና እየገቡ ኖሯል። በዚህ መልኩ የበለጠ እየተሰባሰቡ መጡ። የክርስቲያን ቤትና ሆቴልም እየተመረጠ መቃጠል ተጀመረ። 'ነፍጠኛ አንድም እንዳይቀር' እያሉ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ጀመሩ። ስቃይ ነበር። መከላከያ ብዙ ጉዳት ከደረሰ በኋላ ነበር የመጣው። እኔ እዚሁ ተወልጄ ያደግሁ ነኝ። ምን እንዳደረግን አልገባኝም" – አበበች ፈለቀ፣ ከጥቃቱ ሸሽታ በመጠለያ የምትገኝ የዴራ ነዋሪ።

"ልጄን አርደው ነው የገደሉት። አስከሬን እንኳ ማንሳት አልቻልንም ነበር። በዕለቱ የሆነውን መናገር ይከብዳል። አሁንም ይዝቱብናል። 'ከመጠለያ ውጡ' ይሉናል። መንግሥት አጥፊዎችን ይቅጣልን። ገዳዮች ተቀጡ ሲባል ነው መስማት የምፈልገው" – ደረጀ ፈለቀ፣ የተጎጂ ወላጅ አባት።



"ሰኔ 22 ለ23 አጥቢያ ስምንት ሰዓት ገደማ ነበር ጩኸት የሰማሁት። 'ከቤትሽ ቶሎ ውጭ፤ ቤት እያቃጠሉ ነው' ብለው ደወሉልኝ። መሣሪያ ይተኩሱ ነበር። ቆንጨራ፣ ገጀራም ይዘው እየጮሁ ይሯሯጣሉ። ኦሮምኛ ቋንቋ አውቃለሁ፤ 'ምን ሆናችሁ ነው?' አልኳቸው። 'ሀጫሉ ሞቷል' አሉኝ። ወደቤቴ ተመልሼ ከባለቤቴ ጋር ቤታችንን ዘግተን ተቀመጥን። ወዲያው ቤት መጥተው መደብደብ ጀመሩ። እንደምንም መስኮት ሰብረን ልጆቼን ይዤ ወጣሁ። ቤቴ እና ወፍጮ ቤቴ ተቃጠሉ። ልጆቼን ግን በእግዚር ቸርነት ከቃጠሎ አድኛለሁ" – እንዬ ቸሩ።

"እኔ ከዚህ በኋላ እዚህ ከተማ በሰላም የሚያኖሩን አይመስለኝም። አሁንም ስጋት አለብን። አስተዳደሮቹ ሁሉም ሙስሊሞች ናቸው። ሙስሊም ባለሀብቶች የጥቃቱ ደጋፊ የሆኑ አሉ። ወጣቶችን ከገጠር ጭኖ ያመጣቸው ማን ነው? ደግሶ የሚያበላቸውስ ማን ነበር? አሁንም ድረስ ያልተያዙ አጥፊዎች አሉ። መንግሥት ስጋታችን አልገባውም? አራት ሰዎች ናቸውኮ የታረዱብን። አርደው ቱቦ ውስጥ ነው የጣሏቸው። በአስከሬን ነው የተጫወቱት። የተቆራረጠ የሰው ልጅ አካል ይዘው ነው ሲጨፍሩ የነበሩት። መከላከያ ከመጣ በኋላ ነው አስከሬን ተነስቶ የተቀበረው። ደካማ እናቴን ይዤ ለመውጣት ያየሁትን መከራ አሁን ማስታወስ አልፈልግም" – ወገኔ ግርማ፣ የዴራ ከተማ ነዋሪ።

በዴራ ከተማ 76 ቤቶች ተቃጥለዋል። ከ50 በላይ የንግድ ቤቶችም ተቃጥለዋል። ከወደሙ ሆቴሎች መካከል የዶ/ር ናደው ተ/ጻድቅ ንብረት የሆነው "ምዕራፍ ሆቴል" ይገኝበታል። ዶ/ር ናደው ሆቴላቸው የተቃጠለው 12፡30 ጠዋት መሆኑን ገልጸዋል። ሆቴላቸው በአንድ ጊዜ አራት

የሰርግ ድግሶችን ማስተናገድ የሚችል፣ በ2000 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ነበር።

በዴራ ከተማ የተገደሉ ሰዎች ዝርዝር፡-

መርገን ሲነጋ



መርሻ ደረጀ

ፈይሳ (ያባታቸው ሥም ያልታወቀ

ሰለሞን አበራ (በምዕራፍ ሆቴል አርፈው የነበሩ ከሮቤ የመጡ እንግዳ)

በዴራ ከተማ የተፈፀመው ጥቃት ሃይማኖትን እና ብሔርን የለየ ("ነፍጠኛ" እየተባለ) ሥም ዝርዝር ተይዞ የተፈፀመ ስለመሆኑ ተጎጂዎቹ ገልጸዋል። የዶዶታ ወረዳ ፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ ሃይደር እና አንዳንድ ተጠርጣሪዎች መያዛቸውን ተጎጂዎቹ ቢናገሩም፣ ከሌላ ወገን ማረጋገጥ አልተቻለም። ሆኖም፣ የጥቃቱ ተሳታፊዎች በሙሉ ባለመያዛቸው ተጎጂዎቹ አሁንም ሌላ ጥቃት ይፈፀምብናል በሚል ስጋት ላይ ናቸው።

(በዴራ ከተማ በነበረው ቃጠሎ ሲሊንደር ፈንድቶ ሁለት ጥቃት አድራሾች መሞታቸውን ነዋሪዎች ገልጸዋል። በተጨማሪም የኦሮሚያ ክልል ልዩ ኃይል አመፁን ለመቆጣጠር በተኮሰው ጥይት የተገደሉ መኖራቸውን አክለው ገልጸዋል። ሆኖም፣ ይህን መረጃ ከአካባቢው አስተዳደር ማረጋገጥ አልቻልኩም።)

## አሰላ

በአሰላ ከተማ ንብረትነቱ አቶ መስፍን ጥበቡ የተባሉ ግለሰብ የሆነ የእንጨት ሥራ ፋብሪካ በቃጠሎ እንዲወድም ተደርጓል። በቃጠሎው ከ12 ሚሊዮን ብር በላይ ንብረቱ እንደወደመ አቶ መስፍን ገልጸዋል። ቢሯቸውም ተቃጥሏል።

"ተወልጄ ያደግሁት አሰላ ከተማ ነው። ኦርቶዶክስ በመሆኔና ቤተክርስቲያን ታግዛለህ ተብዬ ነው ተደጋጋሚ በተጠና ሁኔታ ጥቃት የሚፈፀብኝ። ጥቃት አድራሾቹ ከገጠር በመኪና ተጭነው የመጡ ናቸው። የአካባቢው ኅብረተሰብ ቃጠሎውን ሊያጠፋ ሲል ፖሊስ ነው 'ወደ እሳቱ መጠጋት አይቻልም' እያለ የከለከለው። ፖሊስ እና የአካባቢው አስተዳደር ተባባሪ ነበር። የቀበሌው ሊቀመንበር ዋና ተሳታፊ ነበር። በመኪና ተጭነው የመጡትን አቅጣጫ አሳይቶ፣ መለስ ብሎ ልብስ ቀይሮ ነበር ወደ ሕዝቡ የተቀላቀለው። ግልጽ ትብብር ነው ያደረገው። አሁን ታስሯል መሰለኝ። ይሄ ፋብሪካ ውድመት ሲፈፀምበት አሁን ለ2ኛ ጊዜ ነው። ጥቅምት 12/2012ም አቃጥለውብኝ እንደገና በብድር ነው ሥራ አስጀምሬው የነበረው" – አቶ መስፍን ጥበቡ፣ ንብረት የወደመባቸው

የእንጨት ፋብሪካው ለ40 ሰዎች ቋሚና ለ60 ሰዎች ጊዜያዊ ሥራ የፈጠረ ነበር። አቶ መስፍን አሁንም ስጋት እንዳለባቸውና ቤታቸው እንደማያድሩ ገልጸዋል። መኖሪያ ቤታቸውም በዕለቱ ተዘርፏል። "ነፍጠኛ፣ የምኒልክ ወገን" እያሉ ነው ጥቃቱን ያደረሱት ብለዋል።

## ገደብ፤ አሳሳ

በምዕራብ አርሲ ዞን ገደብ አሳሳ በሰዎች እና ንብረት ላይ ጥቃት ከደረሰባቸው ሥፍራዎች አንዱ ሲሆን፣ በ11 ወረዳዎች ጥቃት ተፈፅሟል። በአሳሳ ከተማ ብቻ 3 ወንዶች እና አንዲት ሴት፣ በድምሩ በ4 ሰዎች ላይ አሰቃቂ ግድያ ተፈፅሟል። ግድያው አንገት በማረድ፣ ሰውነት በመቆራረጥ፣ በስለት ደጋግሞ በመውጋት እና በጥይት የተፈፀመ ነው። በአሳሳ ከተማ የተገደሉ ሰዎች ዝረዝር፡-

ተፈሪ በላይነህ

መጠሪያ ላቀው

ስንቅነሽ ገብረየሱስ

ታምራት አዱኛ ናቸው።

ከእነዚህ መካከል በከተማዋ ተወልደው ያደጉት የ87 ዓመት አዛውንቱ አቶ ተፈሪ በላይነህ እና ባለቤታቸው ወ/ሮ ስንቅነሽ ገብረየሱስ በቤታቸው ተቀጥቅጠው የተገደሉ ሲሆን፣ የድርጊቱ ፈፃሚዎች አስከሬናቸውን በመቆራረጥ መንገድ ላይ ጎትተዋል። አስከሬናቸው የተነሳውም ከሰዓታት በኋላ የመከላከያ ኃይል መድረሱን ተከትሎ ነበር።

ወጣት ታምራት የተገደለው ሰኔ 24 ቀን 2012 በጩቤና በገጀራ ነው። ይህም አመፁ በከተማዋ ለሁለተኛ ቀን ቀጥሎ ስለነበር ነው።

በገደብ አሳሳ ሰኔ 23 ቀን 2012 ወጣቶች ፖሊስ ጣቢያ በር ጎማ ሲያቃጥሉ ፖሊስ በዝምታ ይመለከት እንደነበር ተጎጂዎች ተናግረዋል። በዚህም ጥቃቱ የአካባቢው አስተዳደር እና ፖሊስ ይሁንታ ያለበት ነበር ሲሉ ገልጸዋል። ጥቃት የደረሰባቸው ሥም ዝርዝር ተይዞ "ነፍጠኞች" (በተለይ ክርስቲያኖች) ላይ ነበር።

በከተማዋ ዝርፊያ እና ቤት ቃጠሎም ተፈፅሟል። ቤተክርስቲያንን በመርዳት የሚታወቁ ሰዎች ዋና ዒላማ ነበሩ – ተጎጂዎች እንደሚሉት። ጥቃት አድራሾቹ ከገጠር እንዲመጡ የተደረጉም ይገኙበታል። በአሳሳ የተፈፀመው ጥቃት የጀመረው ጠዋት 12፡00 ሰኔ 23 ቀን 2012 ነበር።

በጥቃቱ ማግስት ከ300 በላይ ከጥቃቱ የተረፉ ሰዎች በአሳሳ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ተጠልለው ነበር። አሁን ላይ ከአካባቢው በመልቀቅና ከወዳጅ በመጠጋት ብዙዎች ከመጠለያ ወጥተው ቁጥራቸው ቀንሷል – የደብሩ አስተዳዳሪ እንደተናገሩት። በቤተክርስቲያን የተጠለሉትም እስካሁን ጥቃት ይደርስብናል የሚል ስጋት አላቸው።

(በአሳሳ ከተማ አመፁን ለመቆጣጠር በነበረው ተኩስ የተገደሉ ሰዎች መኖራቸው ነዋሪዎች ቢገልጹም ከአስተዳደሩ ማረጋገጥ አልቻልኩም።)

## ባሌ ሮቤ

ሮቤ ከተማ በሰዎች ላይ ጉዳት አልደረሰም። ሆኖም፣ አንድ መኖሪያ ቤት እና 3 ንግድ ቤቶች ተቃጥለዋል። ንግድ ቤቶቹ ጥቅምት 12 ቀን 2012 በተነሳው አመፅም ተቃጥለው ነበር። በጥቅምቱ ጥቃት ወቅት ንብረታቸው የወደመውና ተጎጂዎች ሆነው ሳለ እስካሁንም ያለፍርድ የታሰሩ እንዳሉ አቶ ሚሚያ ባልቻ የተባሉ የጉዳቱ ሰለባ ገልጸዋል።

"ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ስለሆንሁ ብቻ ሁለት ጊዜ ቤቴ ተቃጥሏል። ቤተክርስቲያን ታሠራለህ ተብሎ የታሰረም አለ። ጥቅምት የታሰሩ እስካሁን አልተፈቱም። በዚያ ወገን ደግሞ 'ቤታችሁን ያቃጠልነው እኛ ነን' እያሉን እስካሁን ያልተጠየቁ አሉ። ምን እየተሠራ እንደሆን አይገባኝም። ይሄው 7 ልጆችን ይዤ በችግር ላይ አለሁ። አሁንም መቼ እንደሚጎዱን አላውቅም። ስጋት ላይ ነን" – አቶ ሚሚያ ባልቻ፣ ንብረት የወደመባቸውና አቶ ተካ አሰፋው የተባሉ ባለቤታቸው የታሰሩባቸው።

ሮቤ ከተማ ጥቅምት ላይ ከተፈፀመው ጥቃት አንፃር ሲታይ የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ የተፈፀመው ጥቃት ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ነዋሪዎቹ ገልጸዋል። ከዚህ በፊት ጥቅምት 13 እና 14/2012 በሮቤ እና ዲንሾ ከተሞች አምስት ሰዎች ተገድለው እንደነበርም ያስታውሳሉ። እነዚህም፡-

በላይ አደሬ

እሸቱ ጌታሁን

ዳምጠው ዘርፉ

ተስፋዬ ድሪባ

ታምራት በቀለ ነበሩ።

በወቅቱ የነበረው የንብረት ውድመትም ከባድ ነበር – ብለዋል ነዋሪዎች።

ባሌ ጎባ

በባሌ ዞን ጎባ ከተማ በሰው ሕይወት ላይ የደረሰ ጉዳት የለም። ሆኖም፣ በከተማዋ ታዋቂ የሆነው "ይልማ ሆቴል" በቃጠሎ ወድሟል። የሆቴሉ ባለቤት የሆኑት አቶ ተስፋዬ ይልማ እንዳሉት "ይልማ ሆቴል" 33 ቋሚ ሠራተኞች ነበሩት። ሠራተኞቹ ለጊዜው መሰናበታቸውን ተናግረዋል። ሆቴሉ ከ1950ዎቹ ጀምሮ አግልግሎት የሰጠ ነበር። መልሶ ሥራ ለማስጀመር ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ይጠይቃል ብለዋል – አቶ ተስፋዬ።

"ጥቃቱ ሲፈጸም ፖሊስ መቆጣጠር ይችል ነበር፤ መከላከልም ይችል ነበር። የባሌ ዞን ፖሊስ መምሪያኮ እዚሁ ከተማችን ውስጥ ነው ያለው። ሆኖም፣ ፖሊስ ምንም አላደረገም። ይሄ በጣም ያሳዝነኛል" – አቶ ተስፋዬ ይልማ

ከባድ ጉዳት የደረሰበት "ይልማ ሆቴል" ይሁን እንጂ፣ በጎባ ከተማ መስታወት መሰባበርን ጨምሮ በ46 ሱቆችና ቤቶች ላይ ቀላል ጉዳት ደርሷል።

ባሌ አጋርፋ

በባሌ ዞን ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው አካባቢዎች ዋነኛው አጋርፋ ወረዳ አምቤቱ ቀበሌ ይገኝበታል። ከጉዳቱ ተርፈው በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ኮሌጅ ት/ቤት ተጠልለው የሚገኙ ሰዎች በርካታ ናቸው። ተጎጂዎቹ እንደሚሉት የተፈናቃዮች ቁጥር 1253 ሲሆን፣ የአጋርፋ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ኃላፊ ሽመልስ ቶሎሳ በበኩላቸው ተፈናቃዮች 1144 ናቸው ብለዋል። በአጋርፋ አምቤቱ ቀበሌ 5 ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል። መኖሪያ ቤቶች፣ ወፍጮ ቤቶች፣ ሞተር ብስክሌቶችና ሌሎች ንብረቶች ተቃጥለዋል። የንብረት ዝርፊያ ተፈጽሟል።

በአጋርፋ አምቤቱ የተገደሉ ሰዎች ዝርዝር፡-

አስቻለው አባቡ

አስፈራ ትርፌ

ሰለሞን በላይነህ

ኃይሌ ጌታቸው

ትዕግስት አስራት ናቸው።

እንደተነገረኝ 'አስቻለው አባቡን አንገቱን አርደው፣ ዓይኑን አውጥተው አቃጥለውታል። ኃይሌ ጌታቸው አንገቱን አርደው ገድለው ጥለውት አስከሬኑን አላስነሳም፣ እዚህ አትቀብሩም በሚል ከልክለው አካሉን አውሬ በልቶት መከላከያ ከደረሰ በኋላ የተቆራረጠ አካል ተሰብስቦ በ3ኛ ቀኑ ነው የተቀበረው። አስፈራ ትርፌ እና ሰለሞንም በተመሳሳይ ታርደው የተገደሉ ናቸው።'

"ሰለሞን ባለቤቴ ነው። ልጆችም ወልደናል። እሱም እኔም ኦሮሞዎች ነን። ነገር ግን 'ክር ያሰረ ኦሮሞ አናውቅም' እያሉ ነው ያሳደዱን። 'ኦሮሚያ ሳውዲ አረቢያ ናት' ይሉ ነበር። ባለቤቴ ሰለሞን 'ክሬን አልበጥስም' ብሎ ነው የታረደው። አራት ልጆቻችንን ይዤ እንዲህ ሆኜ ቀረሁ። 'አብሮን የሰገደ ብቻ ነው ኦሮሞ' ይላሉ" – የኔነሽ ማሞ፣ የሟች ባለቤት።

"እምነት ተኮር ጥቃት ነው የነበረው። እዚህ ሕይወታችንን ለማትረፍ ነው የተጠለልነው። ቃጠሎ እና ዝርፊያ ነበር። ክርስቲያኖች ብቻ እየተለዩ ነው የተጎዱት። ሙስሊሞች በመከላከል ተብሎ ሁለት ተጎድተዋል መሰለኝ።... ክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ከባድ ነው። ሰው ተገድሎ ዓይኑ እየወጣ ብዙ ግፍ ደርሷል። አስከሬን የሚያነሳ እንኳን አልነበረም። መከላከያ ከመጣ በኋላ ታጅበን ነው አስከሬን የሰበሰብነው። ጦር፣ ገጀራ፣ ሌላም ይዘው ነበር። ፖሊስ አልደረሰልንም ነበር። ዕቅድ ነበራቸው መሰለኝ። ከባድ ነበር። እኛን ለመከላከል የተባበሩ ሙስሊሞች ነበሩ። በእነሱ ነው እኛ የተረፍነው" – ወጣት ኪያ ጣሰው፣ ተፈናቃይ።

"ከመስከረምና ጥቅምት ጀምሮ ክርስቲያኖችን በመስደብ፣ በማስፈራራት ያዋክቡ ነበር። ቤተክርስቲያን የሚሔዱትን፣ ክር ያሰሩትን ይሳደባሉ። አዝመራና የቀንድ ከብቶች ይዘረፉሉ። ችግሩ የቆየም ነው። ሰኔ 23 የሆነው ድርጊቱ ነው፤ ሐሳቡ ቆይቷል ባይ ነኝ። ሟች ኃይሌ ጌታቸው ዘመዴ ነው። እኔ ገና ወጣት ነኝ፤ በዚህ ዕድሜዬ የተቆራረጠ አካል ሰብስቤ እንድቀብር ተገድጃለሁ። በጣም አሰቃቂ ነበር። እኔም 'ይታረድ' ተብዬ ሥም ዝርዝር ወጥቶብኛል። ፌስቡክ ላይም ጽፈውብኛል። ክርስቲያን ስለሆንኩ ነው፤ 'ነፍጠኛ' ይላሉ። እኔ ተወልጄ ያደግሁት እዚህ ነው። የት ሂድ ይሉኛል?" – ወጣት ጎሳ ታደረገ፣ ተፈናቃይ።

ከጥቃቱ በመሸሽ ከአንድ ወር በላይ በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ኮሌጅ ተጠልለው የሚገኙት ተፈናቃዮች በመንግሥት በኩል በቂ ዕርዳታ እየተደረገላቸው አለመሆኑን ገልጸዋል። አሁንም የደኅንነት ስጋት አለባቸው። አንዳንድ ጥቃት አድራሾች የታሰሩ ቢሆንም፣ አመፀኞችን በገንዘብና በሥልጣን ላይ ሆነው የሚደግፏቸው ግን አልተያዙም ይላሉ ተፈናቃዮች። ሌላ ጥቃት ሊፈፀም እንደሚችልም ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

የአጋርፋ ወረዳ የብልፅግና ፓርቲ ኃላፊ ሽመልስ ቶሎሳ በበኩላቸው በወረዳው 347 ተጠርጣሪዎች መያዛቸውን ገልጸዋል። ከእነዚህ መካከል 14 የፖሊስ አባላት ሲሆኑ፣ 7ቱ ደግሞ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ናቸው። ሽመልስ ጥቃቱ 'ሃይማኖትም፣ ብሔርም ተኮርም ነበር' ለማለት እንደማይችሉ፣ 'ነገር ግን ሁኔታው ፖለቲካዊ እንደነበር' ተናግረዋል።

የዘገባው ውስንነቶች

ይህ ዘገባ የተዘጋጀው በኢ.አ.ተ.ቤ.ክ. የካሕናትና ምዕመናን ኅብረት የጉዞ ፕሮግራምና ትኩረት የተገደበ በመሆኑ መረጃዎችን ከተለያዩ ወገኖች ለመሰብሰብ ውስንነት ነበረው። በዚህ ዘገባ የአጋርፋ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ኃላፊን ለማነጋገር ከመቻሌ በስተቀር በመንግሥት ወይም በገዢ ፓርቲው በኩል፣ ወይም ከፖሊስ ያለውን መረጃ ከየአካባቢዎቹ ለመሰብሰብና ለማጣራት ጊዜና ሁኔታው አልፈቀደልኝም።

በተጨማሪም፣ ምንም እንኳ ጉዞው በአምስት የፌድራል ፖሊስ አባላት እጀባ የተደረገ ቢሆንም፣ የፀጥታ ስጋት ስለነበር በከተሞቹ በነፃነት ተንቀሳቅሶ ተጓዳኝ መረጃዎችን መሰብሰብ አዳጋች ነበር። የጉዳት ሰለባ ሥፍራዎችንም ተዘዋውሮ ለመመልከት ከጥቂቶች በስተቀር አልተቻለም። ለምሳሌ፣ አጋርፋ በመጠለያ ካሉ ተፈናቃዮችና የጉዳቱ ሰለባዎች መረጃ ከመሰብሰብ ያለፈ፣ ጉዳቱ የደረሰባትን አምቤቱ ቀበሌ ተገኝተን መመልከት አልቻልንም።

ለዘገባው የዋሉ የመረጃ ምንጮች

የአርሲ ዱራ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ

አቶ ደረጀ ፈለቀ (በጥቃቱ ልጃቸውን ያጡ)

ወ/ሮ አበበች ፈለቀ (ተፈናቃይ)

አቶ እንየ ቸሩ (ከጥቃቱ የተረፉ)

አቶ ወገኔ ግርማ (ከጥቃቱ የተረፉ)

ቀሲስ ከፍያለው (የቤተክርስቲያን አገልጋይ)

ዶ/ር ናደው ተ/ጻድቅ (ሆቴል የወደመባቸው)

አቶ መስፍን ጥበቡ (የእንጨት ፋብሪካ የወደመባቸው)

የአሳሳ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ

ዶ/ር ንጉሡ ለገሰ (የካኽናትና የምዕመናን ኅብረት መሪ)

የሟች ስንቅነሽ እና የባለቤታቸው መጦሪያው ቤተሰቦች

አቶ ተስፋዬ ይልማ (ሆቴል የወደመባቸው)

አቶ ማሚያ ባልቻ (ንብረት የወደመባቸውና ባለቤታቸው የታሰረባቸው)

አቶ ሽመልስ ቶሎሳ (የአጋርፋ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ኃላፊ)

አቶ ታደሰ ኢድአ (ተፈናቃይ)

አቶ የባሌ አገረ ስብከት ኃላፊ

ወጣት ኪያ ጣሰው (ተፈናቃይ)

ወጣት ጎሳ ታደረገ (ተፈናቃይ፣ ዘመድ የተገደለበት)

ወ/ሮ የኔነሽ ማሞ (ባለቤታቸው የተገደለባቸው)

በተጨማሪም፡- በቦታው በመገኘት የተደረገው ምልከታ ትልቅ የመረጃ ግብዓት ሆኗል። ፎቶዎችና ቪዲዮዎችንም ማስቀረት ተችሏል።

# አዲስ አበባ የአዲስ አበቤ



ኢንጂነር ጌታነህ ባልቻ (የባልደራስ የፖለቲካ ጉዳዮች ሓላፊ)

ከተማችን አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መዲና፣ የአፍሪካ መዲና፣ የተለያዩ የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ነች። ከ150 በላይ የተለያዩ የዲፕሎማቶች መናኸሪያ፣ ቀደምት የአፍሪካ ታጋዮች ፀረ-የቅኝ አገዛዝ ትግል ጥንስስ ተዛንቆ ውቧ ከተማችን የገጠማትን ፈተና እና ለመወጣት የምታደርገውን ትግል ለመቃኘት ታስቦ የተዘጋጀ ጽሁፍ ነው።

የአዲስ አበባ ምስረታ ከዳግማዊ ምኒልክም አልፎ ረዥም ዘመን እስከ አፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የሚዘልቅ እንደሆነ ፕሮፌሰር ሐብታሙ ተገኘ ‹በራራ- ቀዳሚት አዲስ አበባ› በተሰኘው ጥናታዊ መፅሐፋቸው አብራርተዋል።

በአጼ ምኒልክ በ1894 ዓ.ም የመልሶ ማልማት ሥራዋ ከተጠናቀቀ ወዲህ ብዙ ሂደቶችን አሳልፋለች። ዘመናዊ ለማድረግ ምኒልክ ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን ያደረጉ ሲሆን፣ ዛሬ ላይ ከእዚህ ደረጃ ለደረሰችበት የላቀ ድርሻ በመቀርቀራቸውም ትውልድ ስማቸውን በመልካም ያነሳል።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የነፍጠኛ ከተማ በሚል በመመደብ፣ ከጉያዋ የሚወጣውን ሃብት ከመቦጥቦጥ ነዋሪዋን በሁለተኛ መንገድ ሲበድሉ ከመቆየት ጋብ ብለው አያውቁም ነበር። የከተማዋን ነዋሪዎች በጥርጣሬ ይመለከት የነበረ ህዝብ ለማሸማቀቅና አንገቱን ለማስደፋት ብዙ ርቀት ተጉዟል። ነዋሪውም የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንገብ ያደረጋቸውን ተጋድሎዎች ማንሳት በቂ ይሆን ነበር። ሆኖም ግን ይህ ጽሁፍ ሊገልጽ ወይም ሊያነሳ የፈለገው ዋነኛ አጀንዳ "አዲስ አበባ የአዲስ አበቤነቷን" በመሆኑ የከተማውን ነፃ መብት፣ ዴሞክራሲ፣ የህግ- የበላይነትና መሰል ጉዳዮች በሌላ ርዕስ እመለስበታለሁ።

አዲስ አበባ የአገሪቱን ከ65% በላይ የኢኮኖሚ አስተዋፅኦ የሚያበረክት፣ 7 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ሕዝብ አላት። የከተማው ነዋሪም ከሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የተሰባሰበ ነው። ሀብታሙም፣ ደሀውም የሚኖርበት የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት፣ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ባህሎች የሚንፀባረቁባት የታላቋ ኢትዮጵያ ብሔራዊነት ማሳያ ቅመም ናት።

የአዲስ አበቤ ስነ ልቦናም በተለያዩ ባህሎች፣ ቋንቋዎች ተከባብሮና ተግባብቶ ማህበራዊ ህይወቱን የሚገፋበት፣ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውን ለመጠቀም ሰፊ እንቅስቃሴ የሚያደርግባት ውህድ ማንነት ያለው "ሰው ሁሉ እኩል ነው" የሚል የከተሜነት አመለካከት የሰረፀበት ህዝብ ነው።

ከዚህ ማንነት ያፈነገጠ በብሔርና በቋንቋ ከፋፍሎ መግዛት ላይ ያተኮረው ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ ይህንን የአዲስ አበቤ ማንነት ለመቅበር ሲሠራ ቆይቷል። በዘር እና አጥንት ቆጥሮ መግዛት ላይ የተቸነከረው ህወሓት/ኢህአዴግ የአዲስ አበቤን ጥያቄ ምንነት እንኳ በአግባቡ የሚዳመጥ ፍላጎት አልነበረውም። ሁሉን ጥያቄ የኢኮኖሚ ለማስመሰል የሚጥረው ስርዓትም የነዋሪውን ውህድ ማንነት ለመበጣጠስ ያልቆፈረው ጉድጓድ፣ ያልማሰው አቀበት አልነበረም። የአዲስ አበቤን ስነ ልቦና ለማፈራረስ ከተማ ንዷል፣ ቅርስ አውድሟል፣ ከተለያየ አካባቢ ህዝብ ወደ ከተማው በማስገባት አስተሳሰቡን ወደ ዘርና አጥንት ቆጠራ ለማጥበብ ሰፊ ጥረት አድርጓል።

ይሁን እንጂ አዲስ አበቤን በስነ ልቦና ሊያጠቁት ከከተማዋ መሀል ሲያርቁት ይብስ አመለካከቱ ጠበቀ። ወደ አዲስ አበባ ከሌላ አካባቢ የመጣው የተስማማው ውህድ ማንነት በመያዝ ይበልጥ ኢትዮጵያዊነቱን ያዘ። አዲስ አበቤነት ለመለመ፤ ጎመራ።

በአገራችን የተካሄዱ እልህ አስጨራሽ ትግሎች የፖለቲካ ትግል መነሻ የሆነችው አዲስ አበባ እጅግ ብዙ የተሳኩም ያልተሳኩም ጥረቶች ተደርገውባታል። ህወሓት/ኢህአዴግ የትግሉሉ ምዕራፍ መጨረሻ የነበረው በትጥቅ ትግል አዲስ አበባን ሲይዝ እንደሆነ እናስታውሳለን።

በአገራችን ህዝብ ትግል ተገፍቶ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ወደ ለውጥ ሲመጣ እና ህዝቡ የሽግግር መንፈስ ሲይዝ ዶ/ር አብይ ለሚመራው ስርዓት "ከጎንህ ነን" የሚል ቀንዲል ከፍ አድርጎ በማብራት አዲስ አበቤን ብሎም ኢትዮጵያን በለውጥ ጎዳና እንዲያስኬዱ በማሰብ እንደነበር የቅርብ ትውስታችን ነው። ዛሬ ሌላውን ተስፋ ተጥሎበት የነበረው በዶ/ር አብይ የሚመራው ስርዓት ህዝብ አሸቀንጥሮ የጣለው የተረኝነት ስሜት ተንበርካኪ ሆኖ አዲስ አበቤ እና አዲስ አበባ ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀዋል።

በአዲስ አበባ ውስጥ አዲስ አበቤን ያማከለ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ፖሊሲም መቀየስም ሆነ ለችግሩ መፍትሄ ለማበጀት ከመጣር ይልቅ፣ በተረኝነት ስሜት አህዴድ/ብልጽግና መሬት በመውረር በህገ-ወጥ መንገድ የከተማዋን ውስን መሬት ተከፋፍለውታል። አዲስ አበቤም ያለበትን ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት እጥረት ለምቅረፍ ከልጆቹ ሆድ፤ ከራሱ ፍላጎት ቀንሶ መግቢያዬ ብሎ ከ15 ዓመት በላይ ሲቆጥብ የነበረውን የጋራ መኖሪያ ቤት ተነጥቆ በተረኛነት ስሜት ተወስዶበታል።

አዲስ አበቤ የኔን ስነ ልቦና ይረዳል፣ መርጨዋለሁ ወይም ለችግሬ የሚቆረቆር የፖለቲካ አመራር በተለይ ላለፉት 30 ዓመታት ማግኘት ሳይችል እንደናፈቀው ቀርቷል። የአዲስ አበቤን ውህድ ማንነት መገንዘብ ያልቻለ የዘርና አጥንት ቆጣሪ ነጋዴዎች በላዩ ላይ እየተቀመጡ በዝብዘውታል። የበይ ተመልካች አድርገውታል። በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካ ተጠቃሚ የሚያደርገው ምንም ተጨባጭ ነገር ሊያገኝ አልቻለም።

የከተማዋ ነዋሪ በምጣኔ ኃብት እንቅስቃሴዎች ላይ ሁለተኛ ዜጋ ተደርጎ ቆይቷል። ለዚህም በአፍሪካ ታላቁ የገበያ አዳራሽ የሚባለውን መርካቶን ብቻ ማየት ታላቅ ማስረጃ ነው። ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን በያዘ ማግስት በትግርኛ ተናጋሪ ነጋዴዎች ተሞልቷል። ዛሬ ደግሞ ተራው የኦሮምኛ ተናጋሪዎች ሆኗል።

የአዲስ አበባ ሕዝብ በኢትዮጵያ የማንነት ፖለቲካ ውስጥ ግን ውክልና የለውም። በፌዴሬሽን ምክር ቤት አልተወከለም። ስለዚህ ጉዳዩ የተጠየቁት ሟቹ ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት «አማራን ሁለት ጊዜ አንወክልም» የሚል ምላሽ መስጠታቸውም የሚታወስ ነው። የዚሁ ጠቅላይ ሚንስትር መንግሥት የአዲስ አበቤን ማሕበራዊ ሕይወት ሲበታትነው ኖሯል። በከተማ ልማት ሰበብ ነዋሪዎች ከሰፈራቸው በማፈናቀልና ጎረቤታሞችን የተለያዩ የከተማዋ ጫፍ እና ጫፍ በማስፈር ተመሳሳይ ስነ ልቦና ያላቸውን ዜጎች በመበታተን ማሕበራዊ ሕይወታቸውን ጎድቷል። ኦሕዴድ/ብልፅግናን ደግሞ ልዩ የሚያደርገው የዜጎችን መኖሪያ ቤቶች አፍርሶ ሰዎችን ሜዳ ላይ መበተኑን እንደ መብት ቆጥሮ በገፍ ማፈናቀሉ ነው።

በጥቂቱም ቢሆን ይህንን ያነሳሁትን የአዲስ አበባን ችግር መፍታት እንዲቻል ነው። ዕለት በዕለት ተደራራቢ ለሆኑት የነዋሪው ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ ስለሚያስፈልግም ነው። የአዲስ አበባ ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት የሚችሉት በአዲስ አበቤ ውህድ ማንነት፣ በዴሞክራሲያዊና ህጋዊ መንገድ የሚመረጥ አስተዳደር እና ሥልጣኑን የሚያነብርበት በህግ የታወቀ ወሰን እና ስርዓት ሲኖረው ብቻ ነው። አዲስ አበቤ የከተማው ባለቤት መሆን አለበት። ለዚህም ህዝብን አስተባብሮ መምራት ጊዜው የሚጠይቀው ወሳኝ ትግል ነው።